

ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 276 ሰኔ 6 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# “ኢትዮጵያ በኢጋድ ጥላ ሥር ለቀጣናው ሰላም መሥራቷን ትቀጥላለች”

- ጠቅላይ ሚኒስትር
ዶክተር ዐቢይ አሕመድ


**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለምሥራቅ አፍሪካ ሰላምና መረጋጋት በኢጋድ ጥላ ሥር ከእያንዳንዱ ሀገር ጋር ተባብራ መሥራቷን እንደምትቀጥል ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

14ኛው የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል ሀገራት የመሪዎች ጉባዔ ትናንት በጅቡቲ ሲካሄድ በቀጣናው ሰላም፣ ደህንነት፣ ልማት እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ውይይት ተካሂዷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በትዊተር ገፃቸው ላይ ባሰፈሩት መልዕክት፤ ከኢጋድ የመሪዎች ጉባዔ ጎን ለጎን “ከሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሀሙድ እና ከኬንያው ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ ጋር መወያየታቸውን ገልጸዋል።

“ኢትዮጵያ በኢጋድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ዩኒቨርሲቲው የባህል መድኃኒቶችን በሳይንሳዊ መንገድ እያዘጋጀ ነው

## - ሦስት መድኃኒቶች በቅርቡ ሙከራ ይደረግባቸዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የባህል መድኃኒቶችን በሳይንሳዊ መንገድ እያዘጋጀ መሆኑን አስታወቀ፡፡ በተያዘው ዓመት በሳይንሳዊ መንገድ የተቀመሙ ሦስት የባህል መድኃኒቶች በሰዎች ላይ ይሞከራሉ ተብሏል፡፡

የደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ንጉስ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በደብረ ብርሃን በተለይ አንኮበር በሚባለው አካባቢ ከቦታው ታሪካዊነት እና ከመሬቱ አቀማመጥ ጋር ተያይዞ በሀገሪቱ

ዩኒቨርሲቲው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ዶክተር ንጉስ ታደሰ

# ዓለም አቀፉ

## ”የቤተሰብ ሬሚታንስ መላኪያ ቀን‘ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰኔ 13 ይከበራል

- ዲያስፖራው ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሦስት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ወደ አገር ቤት ልኳል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-ዓለም አቀፉ ‘የቤተሰብ ሬሚታንስ መላኪያ ቀን’ በአገር አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰኔ 13 ለማክበር ዝግጅት ማጠናቀቁን የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት አስታወቀ፡፡ ዲያስፖራው ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሦስት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ወደ አገር ቤት መላኩን አመልክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ዓለም አቀፉ ‘የቤተሰብ ሬሚታንስ መላኪያ ቀን’ እ.ኤ.አ በ2015 በሰኔ ወር እንዲከበር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውሳኔ አሳልፏል። በዚህም በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም አቀፉ ‘የቤተሰብ ሬሚታንስ መላኪያ ቀን’ ሰኔ 13 ይከበራል፡፡

እንደ አቶ ወንድወሰን ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ከጀርመን ተራድኦ ድርጅትና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቀኑን ለማክበር ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል።

ዕለቱ በዓለም ከ200 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ከሀገራቸው ውጪ የሚኖሩ ሰዎች

ዓለም አቀፉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አቶ ሰዲቃ ስሜ

# ለአገራዊ ምክክሩ ስኬት የአገር ሽማግሌዎች ከፍተኛ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ሊደረግ ለታቀደው አገራዊ ምክክር ስኬት የአገር ሽማግሌዎች ከፍተኛ ሚና መጫወት እንደሚጠበቅባቸው ተገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ የአገር ሽማግሌዎች መማክርት የሽምግልና ዘርፍ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ሰዲቃ ስሜ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአገራዊ ምክክሩ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታዩ ያለመግባባት ችግሮችን እንደሚቀርፍ ይጠበቃል፡፡ ለዚህ ስኬታማነትም የአገር ሽማግሌዎች ከፍተኛ ሚና መጫወት አለባቸው፡፡

ለአገራዊ ምክክሩ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል



ዜና



አቶ ባበክር ሀሊፋ

# በክልሉ የመኸር እርሻ 15 ሺህ ሄክታር መሬት በሩዝ ሰብል ይሸፈናል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በቤንሻንጉል ክልል የመኸር እርሻ አሥራ አምስት ሺህ ሄክታር መሬት በሩዝ ሰብል እንደሚሸፈን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የቤንሻንጉል ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባበክር ሀሊፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ክልሉ የሩዝ ምርት አቅርቦትን በስፋትና በጥራት ለሀገር ውስጥ ገበያ ተደራሽ ለማድረግ፣ የሩዝ ሰብል ምርታማነትን እንደሀገር ለማሳደግ እና ከውጭ የሚገባውን የሩዝ ምርት በሀገር ውስጥ ለመተካት ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው።

ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ከማስቀረት ባሻገር ስንዴን ወደ ውጭ ለመላክ እንደ አገር የታቀደውን እቅድ እውን ለማድረግ በክልል ደረጃ የተጀመረው ሥራ እጅግ ውጤታማ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በተመሳሳይ መልኩ የሩዝ ምርትና ምርታማነት ላይም ከዚህ በፊት ባልተመለደ መልኩ ሰፋፊ እንቅስቃሴ እየተደረገበት ይገኛል። በዚህም በቤንሻንጉል ክልል በ2015/16 የመኸር እርሻ 15 ሺህ ሄክታር መሬት በሩዝ ሰብል ለመሸፈን እየተሰራ ነው ብለዋል።

የቤንሻንጉል ክልል የሰብል ልማትና ጥበቃ ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ ፍቅሩ አቡን በበኩላቸው፤ ከመጪው ሐምሌ ወር አጋማሽ ጀምሮ የቤንሻንጉል ክልል ለመጀመሪያ ጊዜ አሥራ አምስት ሺህ ሄክታር መሬት በሩዝ ዘር ለመሸፈን እየሰራ ነው። ይህ ማለት ግን በክልሉ ሩዝ አይመረትም ማለት አይደለም። ሩዝ በክልሉ ሁለት ወረዳዎች በስፋት ሲመረት የነበረ ሰብል ነው ብለዋል።

የሩዝ ሰብል በሁሉም ወረዳ አልተስፋፋም እንጂ አዲስ ሰብል አይደለም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ይህንን ምርት በሁሉም ወረዳዎች ለማስፋፋት የተለያዩ ሙከራዎች ተደርገዋል። በተደረገው ሙከራ ከ22 ወረዳዎች በ18ቱ ወረዳዎች ሩዝ ማልማት እና ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ተረጋግጧል ብለዋል።

እንደ አቶ ፍቅሩ ገለፃ፤ በቤንሻንጉል ክልል በሐምሌ ወር አሥራ አምስት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሩዝ ዘር የመዝራት ተግባር ይጀመራል። ይህ ሲባል ግን በሁሉም ወረዳዎች እኩል ዘር መዘራት ይጀምራል ማለት አይደለም። ምክንያቱም እንደየወረዳዎቹ መልክዓ ምድር የሚዘራበት ጊዜ የሚለያይ በመሆኑ ነው።

የሩዝ ዘር አቅርቦቱ ከግብርና ሚኒስቴር እና ከግብርና ኢንስቲትዩት እንድናገኝ ሁኔታዎችን እያመቻቸን ነው ያሉት አቶ ፍቅሩ፤ ሩዝ ከዚህ ቀደም በፓዊ እና በዳንጉር ወረዳ የሚመረት በመሆኑ ከወረዳዎቹ ዘር ለመውሰድ ታቅዷል። ህብረተሰቡም የሩዝ ምርት ውጤታማ መሆኑን ከፓዊና ከዳንጉር ወረዳ በመመልከቱ የሩዝ ምርትን በሁሉም ወረዳዎች ለማስፋት የምናደርገውን ጥረት እየደገፈ ነው ብለዋል።

የክልሉ ግብርና ቢሮ በቀጣይ ሳምንት ለአርሶ አደሮችና ለግብርና ባለሙያዎች የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ስልጠናዎችን በዘርፉ ብቁ በሆኑ ባለሙያዎች መስጠት እንደሚጀምርም ገልጸዋል።

# በሀገራዊ ምክክሩ የሚሳተፉ አባላት ምልመላ መድረክ በአራት ክልሎች መካሄድ ጀመረ

**በአዲሱ አደሳ**

ሀዋሳ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ወክለው በምክክሩ የሚሳተፉ አባላት የምልመላ መድረክን በአራት ክልሎችና በአንድ ከተማ መስተዳድር ማካሄድ ጀመረ።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ወክለው በምክክር ኮሚሽን የሚሳተፉ አባላት ምልመላ መድረክ በሲዳማ፣ በሀረሪ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ምዕራብ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ማካሄድ ጀምሯል።

በሲዳማ ክልል እየተካሄደ በሚገኘው መድረክ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ተገኝ ጌጡ(ዶ/ር) ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን መሠረታዊ አላማው አንኳር አንኳር በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት ተደርሶ ሀገሪቱን ወደፊት ማስቀጠልና ወደ ተረጋጋ ሕይወት ማምራት ነው ብለዋል።

የምክክር ኮሚሽኑ የተወሰነ ቡድን ስብሰባ አይደለም ያሉት ኮሚሽነሩ፣ የዛሬው መድረክ አላማም የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎችን በመወከል በምክክሩ የሚሳተፉ አካላትን መመልመል እንደሆነ አስገንዝበዋል።

ምልመላው የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያሳትፍና ሀገራችንን ወደፊት የሚያስቀጥሉበት ነውም ብለዋል።

ችግሮችን በውይይት ከመፍታት ይልቅ ጠብመንጃ ማንገብ አዋጭ አይደለም፤ ኅታች ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ለውይይት በራቸውን የዘጉ ሀገራት ችግራቸውን በጠብመንጃ ለመፍታት እንዳልተቻላቸው ከሶሪያና መሰል ሀገሮች መማር ይቻላል ነው ያሉት።



የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከፍተኛ ባለሙያ የሆኑት ጥበቡ ታደሰ በበኩላቸው፤ ኮሚሽኑ የተቋቋመው በሀገር ደረጃ በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ያሉ ልዩነቶችን ለማስታረቅ ነው ብለዋል።

በመድረኩ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ተሳታፊዎች የተገኙ ሲሆን፤ የእስካሁን የኮሚሽኑ ሂደት ውጤታማ መሆኑም ተገልጿል።

መድረኩም ህብረተሰብን ወክለው በምክክር ኮሚሽኑ የሚሳተፉ ሁለት ተወካዮችንና አንድ ተጠባባቂ በመምረጥ የሚጠናቀቅ ይሆናል።

# መስማት የተሳናቸው ዜጎች መኪና እንዲያሽከረክሩ መመሪያ ቢወጣም ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- መስማት የሳተሳናቸው ዜጎች መኪና እንዲያሽከረክሩ የሚፈቅደው መመሪያ ተግባራዊ መሆን አለመቻሉን የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር ገለጸ። የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በበኩሉ ችግሩን ለመቅረፍ ኮሚቴ ማቋቋሙን አሳውቋል።

በኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ጳውሎስ ካሱ እንደተናገሩት፤ መስማት የተሳናቸው መኪና እንዲያሽከረከሩ መንግስት በመመሪያ ቢፈቅድም፤ አፈጻጸሙ ላይ ግን ክፍተት ስላለበት ተግባራዊ መሆን አልቻለም።

ዶክተር ጳውሎስ እንዳመለከቱት፤ መመሪያው መስማት ለተሳናቸው መብት ቢሰጥም መንጃ ፈቃድ ለማግኘትም ሆነ ለማሽከርከር ግን በአካባቢያቸው ያለውን ድምጽ ወደ ጽሁፍ የሚቀይር ቴክኖሎጂ የተገጠመለት ተሽከርካሪ እንደሚያስፈልግ ስለሚያዝ መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥሯል።

አብዛኛዎቹ የመንጃ ፈቃድ ትምህርት ቤቶችም የተጠየቀውን ቴክኖሎጂ የሚያሟላ ተሽከርካሪ ስለሌላቸው መስማት የተሳናቸው ዜጎች መንጃ ፈቃድ ማግኘትም ሆነ ማሽከርከር አልቻሉም ብለዋል።

ዶክተር ጳውሎስ እንደገለጹት፤ ተሽከርካሪውን የተወሰኑ አቅም ያላቸው ሰዎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ ።ነገር ግን በታክሲ ስራ ተሰማርተው እራሳቸውን በገቢ ለማጠናከር የሚፈልጉ መስማት የተሳናቸው ዜጎችን ያማከለ ባለመሆኑ መመሪያው እንዲስተካከል ተጠይቋል።

የሌሎች አገራትን አሰራር ስንመለከት እንደዚህ አይነት መመሪያ እና ሕግ ያለበት አገር የለም ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በኢትዮጵያ መመሪያው ከወጣ አራት አመት ቢሆንም እስካሁን ድረስ ተግባራዊ አልተደረገም ብለዋል።



አቶ ከድልማግስት ኢብራሂም



ዶክተር ጳውሉስ ካሱ

በአገሪቱ መስማት የተሳናቸው መኪና እንዲያሽከረክሩ ካለፉት 40 ዓመታት ጀምሮ ጥያቄ ሲቀርብበት ቆይቷል ያሉት ዶክተር ጳውሎስ፤ በ2011 ዓ.ም መንግስት ለጥያቄዎቹ ምላሽ መስጠት ተችሎ ነበር፤ ሂደቱ ላይ ጥሩ ነገሮች ቢኖሩም በመመሪያው አፈጻጸም ላይ ክፍተቶች በመታየታቸው ሊታረም ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

መመሪያ ሲወጣ መስማት የተሳናቸው ማህበር ተሳትፎበት እና ተወያይቶበት የወጣ አልነበረም ያሉት ዶክተር ጳውሎስ፤ መመሪያው የአገራችንን የአቅም ሁኔታ እና መስማት የተሳናቸውን አቅም ያገናዘበ አይደለም ሲሉ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸውን ዜጎች በተመለከተ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ተግባራዊነት አለማድረጓም ጥያቄ እንደሚያስነሳባት ጠቁመዋል።

በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የሕዝብ ትራንስፖርት አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ጉዳዮች መሪ አስፈጻሚ አቶ ከድልማግስት ኢብራሂም በበኩላቸው፤ በጉዳዩ ላይ የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር ጋር በመወያየት ችግሩን ለመፍታት የሚረዳ ከሚቴ መቋቋሙን አስታውቀዋል።

ችግሩን ለመቅረፍ የተቋቋመው ኮሚቴ ውስጥ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትርና የአዲስ አበባ ከተማ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ባለስልጣንም መካተታቸውን ገልጸዋል።

መስማት የተሳናቸው የመንጃ ፈቃድ በሚያወጡበት ወቅት መስማት ከሚችሉ ሰዎች በተለየ መልኩ እንዲሰለጥኑ በሚል መመሪያው መውጣቱን ያስታወሱት አቶ ከድልማግስት፤ መመሪያ የሚያስፈልገው ችግሮችን ለማስተካከል በመሆኑ ክፍተቶቹን ለመቅረፍ ጥረት ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በመሆኑም የተቋቋመው ኮሚቴ በቀጣይ የተለያዩ ስራዎችን በማከናወን ችግሮችን የመለየትና የመፍትሄ አቅጣጫ የማስቀመጥ ኃላፊነቱን ይወጣል ሲሉ ተናግረዋል።

# ዩኒቨርሲቲው አካባቢ ጥበቃ ላይ በመሥራት የዓባይ ውሃን ከደለል እየተከላከለ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አካባቢ ጥበቃ ላይ በመሥራት የዓባይ ተፋሰስን ከመራቆትና ከመሸርሸር እና ወንዙን ከደለል የመጠበቅ ስራ በማከናወን ላይ መሆኑን የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ።

የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ ጥናትና ምርምር ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር እሸቱ ወንድሙ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው የአካባቢ ጥበቃ ስራን በስፋት እያከናወነ ነው። በደጋ፣ በቆላ የሚለምዱ ቀርከሃንና ለምግብነት የሚውሉ ችግኞችን በመትከል የአፈር መራቆትንና መሸርሸርን የማዳን ስራ እየሰራ በማከናወን ላይ ይገኛል።

ዩኒቨርሲቲው እያከናወነ የሚገኘው የአካባቢ ጥበቃ ስራ በዋናነት መሰረት የሚያደርገው ወደ ዓባይ ወንዝ የሚሄደውን ደለል መከላከል ላይ ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በዓባይ ተፋሰስ ዙሪያ ያለውን የደጋማ አካባቢ አፈር እንዳይሸረሸር የመጠበቅና የማስጠበቅ ስራዎችን በዩኒቨርሲቲው ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በቆላማ አካባቢዎች የቆላ ቀርከሃን በመትከልና ሌሎችን በማስተባበር የቆላማ አካባቢ የአፈር መጠበቅ ስራዎች እየተሰሩ ነው ያሉት ዶክተሩ፤ የሕዳሴ ግድቡን ከደለል ለመጠበቅ ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ በተናጠልና በጋራ የአካባቢ ጥበቃ ስራን በዓባይ ወንዝ ላይ እያከናወነ እንደሚገኝ አብራርተዋል። ከአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በጋራ እየሰሩ እንደሚገኙም ጠቅሰዋል።



ዶክተር እሸቱ ወንድሙ

ዩኒቨርሲቲው ሀሳብ ከማመንጨት ጀምሮ ተቋማትንና የአካባቢውን ነዋሪዎች በማስተባበር የአካባቢ መራቆትን በመጠበቅ የሕዳሴ ግድቡ በደለል እንዳይሞላ የማድረግ ስራ በማከናወን ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የቆላ ቀርከሃንና የቆላ ፍራፍሬዎችን መሰረት በማድረግ ወደ ዓባይ ወንዝ የሚገባውን ደለል የመከላከል ስራ በስፋት እየተሰራ ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ የችግኝ ጣቢያዎችን ማደራጀትና ድጋፍ ማድረግ ተጠቃሽ ነው። በዓባይ ወንዝ ተፋሰስ ዙሪያ በአካባቢው በስፋት የማዕድን ማውጣት ስራ የሚከናወን በመሆኑ ስርዓት በማስያዝና አቅጣጫ በመስጠት ሁሉም አካላት ተሳትፎ እንዲኖራቸው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ እየተከናወነ ይገኛል። ይህም ለአካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል።

ችግኖችን ከማፍላትና ጥናትና ምርምር ከማድረግ ጎን ለጎን ዩኒቨርሲቲው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራን በስፋት በመስራት የዓባይ ተፋሰስ እንዳይራቆት እያደረገ ነው። ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ከሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ተሞክሮ እንዲወስዱና የቆላ ቀርከሃን የማላመድ ስራ እንዲያስፋፉ እየተደረገ ነው። እንዲሁም ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በደጀን ወረዳ ላይ የችግኝ ጣቢያ እያቋቋምን ነው ብለዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን የአርሶ አደሩን ሕይወት ከማሻሻል አንጻር በዩኒቨርሲቲው የሚከናወኑ ስራዎች መኖራቸውን የገለጹት የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዚዳንት፤ በሰሜን ሸዋ ዞን ያሉ አርሶ አደሮች ሕይወት እንዲሻሻል ከፍተኛ የወተት ምርት የሚሰጡ ዝርያዎችን ከደቡብ ኮሪያ በማምጣት የማዳቀል ስራ እየተሰራ ነው። ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ ከ500 በላይ ጥጆች በዞኑ ተወልደዋል። ዩኒቨርሲቲው የወተት ጥራትን የማስጠበቅ ስራንና የማዳቀል ስራን በከፍተኛ ደረጃ እየሰራ ነው። ብዛትና ጥራት ያለው የወተት ምርት እንዲኖር በማድረግ አካባቢው የወተት ኮሪደር እንዲሆን ከፍተኛ ስራ በመሰራት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።



# ኢንስቲትዩቱ ሦስት ሚሊዮን ሀገር በቀል እጽዋትን ለተከላ አዘጋጅቷል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የአየር ንብረት ለውጥን የተላመዱ ሦስት ሚሊዮን የሀገር በቀል ዕጽዋት ችግኞች ማዘጋጀቱን የኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መለሰ ማሪዎ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለዘንድሮው ዓመት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የሚውሉ ሦስት ሚሊዮን የሀገር በቀል ዕጽዋት ችግኞች ተዘጋጅተዋል።

ተቋሙ የአገር በቀል እጽዋትን ማስፋፋት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ እጽዋቶቹ ለብዙ ሺህ ዓመታት በአገሪቱ የቆዩ ስለሆኑ የአየር ንብረት መለዋወጥን የተለማመዱ ናቸው ብለዋል።

ለችግኝ ተከላ ከተዘጋጁ የሀገር በቀል ዕጽዋቶች መካከል የኮሶ ዛፍ፣ ዝግባ፣ ዋርካ፣ ወይራ፣ ጽድ እንደሚገኙበት ገልጸዋል።

ለመድኃኒትነት፣ ለከብት መኖ፣ አበባቸው ለንብ ምግብነት የሚውል፣ ብልን የሚቋቋሙና ለባህላዊ የሽምግልና ስርዓት የሚያገለግሉ የሀገር በቀል ዕጽዋቶች እየለሙ መሆኑን ጠቁመዋል።

አገር በቀል ችግኞቹ የሚዘጋጁት በስፋት በጅማ፣ በሻሸመኔ፣ በሐረር፣ በባሌ ጎባ እና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ ማዕከላት መሆኑን አስታውቀዋል።

ዶክተር መለሰ እንደተናገሩት፤ የሀገር በቀል ዕጽዋቶቹ ለመብቀል ብዙ ውሃ የማይወስዱና የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ የሚረዱ መሆናቸውን ጥናቶች ያመላክታሉ።

ባህር ዛፍን ጨምሮ ከውጪ አገራት የመጡ አብዛኛዎቹ ዕጽዋቶች የከርሰ ምድር ውሃን አሟጦ የመጠቀም አቅማቸው ከፍተኛ ነው ያሉት ዶክተር መለሰ፤ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ተክሎች ሳይንሱ እንደሚያሳየው ለአየር ንብረት ለውጥ ችግር መንስኤ ናቸው ሲሉ አስረድተዋል።

ከጥቅሙ አንጻር አርሶ አደሮችና ተቋማት ሀገር በቀል ዕጽዋትን በስፋት እንዲጠቀሙ የማበረታታት ስራ ይከናወናል ብለዋል።

ሀገር በቀል ዕጽዋቶቹ ለትምህርት ቤቶች፣ ለክፍለ ከተማዎች፣ ለመንግስት ተቋማትና ለአርሶ አደሮች እንደሚቀርብ አስታውቀዋል።

ዳይሬክተሩ እንደገለጹት፤ ኢንስቲትዩቱ የተመናመኑ አካባቢዎችን በመለየት እና የአየር ሁኔታውን በማጥናት የትኛው ተክል ለየትኛው አካባቢ ይስማማል የሚለውን በመለየት እየሰራ ይገኛል።

በአየር ንብረት የተጎዱ አካባቢዎች ላይ ስነምህዳሩ እንዲያገግሙ ለማድረግ ተቋሙ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ላይ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሀገር በቀል ዕጽዋቶች ላይ ትኩረት አድርጎ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እንዲከናወን ባስተላለፉት መልዕክት መሰረት ለሀገር በቀል ዕጽዋቶች ትኩረት መሰጠቱ አበረታች ነው ብለዋል።



ዶክተር መለሰ ማሪዎ

ዶክተር መለሰ እንዳመለከቱት፤ ከዚህ በፊት በየዓመቱ አንድ ሚሊዮን ችግኞች ተዘጋጅተው የሚሰራጩ ሲሆን፤ አሁን ላይ ቁጥሩ ወደ 3 ሚሊዮን ከፍ እንዲል ተደርጓል።



አለሚቱ ኡሙድ

# ህጻናት ዲጂታል ቴክኖሎጂን ሲጠቀሙ እውቀታቸውን በሚያዳብር መልኩ መሆን ይኖርበታል

**ሔለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ህጻናት ዲጂታል ቴክኖሎጂን ሲጠቀሙ እውቀታቸውን በሚያዳብር መልኩ ብቻ መሆን እንዳለበት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አሳሰበ።

በኢትዮጵያ ለ32ኛ ጊዜ የተከበረው የአፍሪካ ህጻናት ቀን "ሰላም፣ ፍቅር፣ እንክብካቤና ጥበቃ ለሁሉም ህጻን" በሚል ሃሳብ ሰሞኑን ተከብሯል።

የአፍሪካ ህጻናት ቀንን አስመልክቶ የህጻናት ዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ ውይይት ሲካሄድ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ አለሚቱ ኡሙድ እንደገለፁት፤ ከኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 52 በመቶ ድርሻ ያላቸው ህጻናት ሲሆኑ፤ መንግስት የህጻናትን መብት፣ ጥቅም እና ደህንነት ማስጠበቅ ላይ ያለበትን ኃላፊነት እየተወጣ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ያለው የህጻናት ዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከአራት ህጻናት አንዱ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆኑን አመልክተው፤ ከ12 እስከ 17 ዓመት እድሜ ክልል ያሉ ህጻናት ለብዙ ጊዜ ተጠቃሚ መሆናቸውን ጥናቱ ያመላክታል ብለዋል።

በዚህም ህጻናት የዲጂታል ቴክኖሎጂን ሲጠቀሙ እውቀትና ክህሎት ለማዳበር፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለመገናኘት፣ ለፈጠራ አጋዥ እድሎችን ለማግኘት፣ የትምህርት መረጃዎችን ለማግኘትና ማህበራዊ ግንኙነትን ለመጠናከር ሊሆን እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ህጻናት የዲጂታል ቴክኖሎጂን በአግባቡ የማይጠቀሙ ከሆነ ለማህበራዊ ሚዲያ ሱስ መጋለጥ፣ በአስተሳሰብ ብስለትና ለነገሮች ያሏቸው አመለካከት መቀነስ፣ ለስነልቦናና ማህበራዊ ጤና ችግሮች መጋለጥ፣ ከቤተሰብ ጋር ያለው መስተጋብር መቀነስ፣ በትምህርት ውጤታማ አለመሆን፣ የማንነት ቀውስ፣ በህይወት አለመረጋጋትና ለመሰል ችግሮች ተጋላጭ እንደሚያደርጋቸው አስረድተዋል።

ዲጂታል ቴክኖሎጂ ህጻናት ላይ የሚያሳድረውን ጫና በመረዳት ለህጻናት፣ ለቤተሰብ እና ለማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ስለችግሩ አሳሳቢነት በስፋት ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል ብለዋል።

ህጻናትን በመልካም አስተዳደግና ስብዕና ለመቅረጽ፣ ለተሟላ እድገታቸው አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ለማሟላት፣ መብትና ደህንነታቸውን የሚያስጠብቁ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎች፣ አሰራሮችን የማውጣት፣ የመተግበር፣ በህጻናት እንክብካቤና ድጋፍ ዙሪያ የሚሰሩ አካላትን የመደገፍና የማበረታታት ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

ህፃናት በመልካም ጤናና ሰብዕና ታንጸው እንዲያድጉ እድገታቸውን ሊያስናክሉ ከሚችሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዲጠበቁ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ በአለም አቀፍ ደረጃ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ህፃናት ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት እያደረሰ እንደሚገኝ የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በአለም አቀፍ ደረጃ ኢንተርኔት ከሚጠቀሙ ሶስት ሰዎች አንዱ ህጻን እንደሆነ በዘርፉ የተጠኑ ጥናቶች እንደሚያመላክቱ ተናግረዋል።

ዜና

# “ኢትዮጵያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በዚህም የጋራ ጥቅሞቻችንን እና ስጋቶቻችንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የጋራ ተግዳሮቶቻችንን ለመቅረፍ በሚያስችሉ ጉዳዮች ኢትዮጵያ ከእያንዳንዱ ሀገር ጋር ተቀራርባ መስራቷን ትቀጥላለች ነው ያሉት።

“ብዙ የጋራ ጥቅሞቻችንን እና ሥጋቶቻችንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የጋራ ተግዳሮቶቻችንን በድል ለመወጣት ኢትዮጵያ ከእያንዳንዱ ሀገር ጋር ተቀራርባ ትሠራለች”ብለዋል።

ኢትዮጵያ በኢጋድ ጥላ ሥር ለቀጣናው ሰላም መሥራቷን ትቀጥላለች ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለምሥራቅ አፍሪካ ሰላምና መረጋጋት የኢጋድ አባል ሀገራት ከምንጊዜውም በላይ ጠንክረው ሊሰሩ እንደሚገባ ገልጸዋል።

የኢጋድ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ወርቅነህ ገበየሁ በበኩላቸው፤ በጉባኤው የሁሉም የሀገር መሪዎች መገኘታቸው ቀጣናውን የሚመለከቱ የጋራ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳያል።

ጉባኤው ወደ ኋላ መለስ ብለን ለማየት፣ ለማሰላሰል፣ የተገኘውን እድገት ለመገምገም፣ እንቅፋቶችን ለመለየት እና ለመፍታት ያስችላል ያሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ ይህም ወደፊት በምን መልኩ መጓዝ እንደሚገባ ይጠቁማል ብለዋል።

የሱዳን ተቀናቃኝ ሀይሎች ጦርነቱን አቁመው ለውይይት እድል እንዲሰጡ ኢጋድ እንደሚሰራም ገልጸዋል።

በጉባኤው የኢጋድ አባል ሀገራት መሪዎች፣ የአፍሪካ ህብረት፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ የአውሮፓ ህብረት እና የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ ተወካዮች ተሳትፈዋል።

ቀጣናዊ ተቋሙ በምስራቅ አፍሪካ እየተከናወኑ ላሉ ስራዎች፣ እየሰጠ ባለው ምላሽ፣ ሌሎች ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ እንደመከሩ ታውቋል።

# ዩኒቨርሲቲው የባህል መድኃኒቶችን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሁሉም አካባቢዎች ሊባል በሚችል መልኩ ለመድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ዕፅዋት የሚገኙበት ሥፍራ ነው።

እነዚህን ዕፅዋቶች በመጠቀም የድሮ አባቶች መድኃኒት ይቀምሙ እንደነበር የጠቀሱት ዶክተር ንጉስ፤ የጥንት የአንኮበር ቤተ መንግሥት በዚያ አካባቢ በመሆኑ ምክንያት እና በጊዜው ሳይንሳዊ መድኃኒቶች እንደልብ የማይገኙ በመሆኑ ለባህላዊ ሕክምና የሚውሉ ዕፅዋት በአካባቢው ሆን ተብሎ እንዲራቡ መደረጉን ጠቁመዋል።

የቤተ መንግሥቱ ሰዎች ሲታመሙ ሕክምና የሚያገኙት ከዚሁ ሥፍራ እንደነበር አስታውሰው፤ አካባቢው ከፍተኛ መሆኑና በአብዛኛው ዓመቱን ሙሉ ዝናብ ማግኘቱ ዕፅዋቱ እስካሁን እንዲቆዩ ማስቻሉን ተናግረዋል።

የዕፅዋቱን ቅመማ እና መድኃኒትነት የሚያውቁ ረጅም ዕድሜ ያላቸው አባቶች እና እናቶች አሁንም በአካባቢው መኖራቸውን እንደ ዕድል በመጠቀም ዩኒቨርሲቲው አብሮ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል። እነዚህ አባቶች እና እናቶች ለማመን የሚከብዱ በሽታዎችን ቅጠል በጥሰው ማዳን የሚችሉ መሆናቸውን ነው ዶክተር ንጉስ የገለጹት።

ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ይህንን በመገንዘብ ሀገር በቀል የሆነውን የአባቶችን ዕውቀት ወደ ዘመናዊ ዕውቀት ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ አባቶች እና እናቶች እስካሁን እየተጠቀሙበት ያለውን የዕፅዋት የመድኃኒት ቅመማ ዩኒቨርሲቲው ፈትሾ አብዛኞቹ ቅመማዎች ውጤታማ ሆነው መገኘታቸውን አስረድተዋል።

የባሕላዊ መድኃኒቶችን የአቀማመም ሥልት በማጥናት ሳይንስ በሚቀበለው መልኩ ለማድረግ የተለያዩ ምርምሮች እየተሠሩ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ሥራው እየተሠራ የሚገኘውም የመድኃኒት ቅመማ ዕውቀቱ ካላቸው አባቶች ጋር በመሆን ነው ብለዋል።

በአጠቃላይ በርካታ መድኃኒቶች በቅመማ እና በሙከራ ደረጃ እየተሠሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ በአይጦች እና በሌሎች ከሰው ጋር ተመሳሳይ የሰውነት ሥርዓት ባላቸው እንስሳት ላይ ሙከራቸው ተጠናቆ በሰው ላይ ሊሞከሩ የተዘጋጁ ሦስት መድኃኒቶች በያዝነው ዓመት ሙከራቸው ይጠናቀቃል ብለዋል።

በሰዎች ላይ ሙከራ ለማድረግ የሰዎች መረጣ መጠናቀቁን እና ወደ ሙከራ ሂደት ለመግባት አስፈላጊው ሥርዓት እየተሟላ መሆኑን አስረድተዋል። መድኃኒቶቹ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ የሙከራ ደረጃዎችን ሲያጠናቅቁ ወደ ምርት እንደሚገቡ ገልጸዋል።

የመድኃኒት መቀመሚያ ዕፅዋቱ እንዳይጠፉ እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው ጠቁመው፤ የዕፅዋት ማዕከል እየተዘጋጀ መሆኑን ተናግረዋል። ለዕፅዋት ማዕከሉ 36 ሄክታር መሬት ርክክብ ተካሂዶ ለመጀመሪያ ዙር በ14 ሄክታር ላይ ስራው ተጀምሯል ብለዋል።

# ዓለም አቀፉ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የቤተሰብ አባሎቻቸውን ህይወት ለማሻሻል የሚልኩት ገንዘብ ያለውን ፋይዳ ለመዘከር ይረዳል ያሉት አቶ ወንድወሰን፤ በተለይም ከሚላከው ገንዘብ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በሚቻልባቸው አማራጮች ዙሪያ ውይይት ይደረጋል ብለዋል።

በተጠናቀቀው የአውሮፓውያን ዓመት ከአገራቸው ውጪ ከሚኖሩ ሰዎች 626 ቢሊዮን ዶላር በዕድገታቸው ወደ ኋላ ቀርተዋል ወደ ሚባሉ ሀገራት መላኩን አመልክተው፤ይህም የቤተሰብን፤የአካባቢውን ማህበረሰብ ህይወት ለማሻሻልና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተያዙትን ዘላቂ የልማት ግቦችን ዕውን ለማድረግ የሚረዳ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ዓለም አቀፉ ‘የቤተሰብ ሬሚታንስ መላኪያ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተቀባይነት ያለው ነው ያሉት አቶ ወንድወሰን፤ የገንዘብ ልውውጥን አስፈላጊነት በማክበር በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው በዓል መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከፍተኛ ሬሚታንስ ከሚቀበሉ ሀገራት መካከል እንደምትመደብ አውስተው፤ባለፉት ዘጠኝ ወራት ዲያስፖራው ሶስት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ወደ አገር ቤት መላኩን ገልጸዋል፡፡

በዓመት በአማካኝ ወደ አራት ቢሊዮን ዶላር ወደ ሀገር ቤት እንደሚልክ ጠቅሰው፤ይህም የዜጎችን ህይወት በማሻሻልና በሀገራዊ ልማት ላይ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

በዕለቱ ሬሚታንስ ድህነትን በመቀነስና የቤተሰቦችን ህይወት ከማሻሻል አንጻር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ፤በዲጂታል ቴክኖሎጂ አማካኝነት ሬሚታንስን ለመላክ እንደ ሀገር ያሉትን አማራጮችና ዕድሎችን የሚዳስሱ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበው ውይይት ይደረግባቸዋል ብለዋል፡፡

ለቤተሰብ የሚላክ የሬሚታንስን ፍሰትና አስተዋጽኦውን ከማሳደግ አንጻር ያሉ ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን ለማግኘት የሚያስችል መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በመድረኩ ላይ የፋይናንስ ዘርፍ ህግ አውጪና ተቆጣጣሪ አካላት፣ የፋይናንስ ተቋማትና የሀዋላ አስተላላፊ ድርጅቶች፣ የዳያስፖራ አደረጃጀቶችና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶች፣ ዓለም ዓቀፍ የልማት አጋሮች እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ተጋባዥ እንግዶች የሚሳተፉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰላም ስምምነቱን የማጽናት ጉዞው በሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ሊደገፍ ይገባል!

ከአፍ የሚወጡ ክፉ ቃላት፣ ከእጅ የሚወረወሩ ፍላጻዎች ወደ ጨለማው ጦርነት ሲያስጉዞ፤ ቀና ንግግሮች፣ መልካም ተግባራትና እሳቤዎች ደግሞ ከጨለማው ጦርነት ወደ ብርሃናማው ሰላም ያደርሳሉ፡፡ ጦርነት ደግሞ ሃብት ንብረትን ያወድማል፤ የተሰራን ያፈርሳል፤ የተዋደደን ይነጥላል፤ ክቡሩን የሰው ልጅ አካልና ሕይወት ይነጥቃል፡፡ በአንጻሩ ሰላም ሰርቶ ሃብት ማፍራትን፣ ገንብቶ መቋጨትን፣ ወልዶ መሳምና አሳድጎ ለቁምነገር ማድረስን፣ ወዳጅነትና ወንድማማችነትን አጠንክሮ በፍቅር ማጽናትን የመሳሰሉ ከፍ ያሉ በረከቶችን ያድላል፡፡

ቀና ሃሳብ፣ መልካም ቃላትና ንግግሮች ከበጎ ምግባር ጋር ሲዳመሩ ደግሞ፤ ድቅድቅ ጨለማ የሆነውን አውዳሚ ጦርነት አስወግደው በቦታው ለሰው ልጆች ብሩህ መንገድ የሆነውን ሰላም ያስገኛሉ፤ ያጸናሉም፡፡ ኢትዮጵያም በተለያዩ ምክንያቶች በጨለማው ጦርነት ውስጥ አልፋ አያሌ ዜጎቿን ተነጥቃለች፤ በትሪሊዮን የሚቆጠር አንጡራ ሃብቷን ለእሳት ዳርጋለች፤ በወንድማማቾች መካከል የነበረውን መልካም ግንኙነት ያሻገር ክፉ ጠባሳንም አዝላለች፡፡

ከእነዚህ ሁነቶች መካከል ላለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ተከስቶ የነበረው ጦርነት ተጠቃሽ ነው፡፡ በዚህም ከፍ ያለ ቁሳዊም፣ ሰብዓዊም ጉዳት ደርሷል፤ ሥነልቡናዊ እና ማህበራዊ ተጽዕኖውም የገዘፈ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁሌ በጨለማ መራመድ፣ በድቅድቅ ውስጥም መዳከር መጨረሻው ጫፍ የሌለው ጥፋትን የሚያስከትል እንደመሆኑ፤ ከጦርነት ለመውጣት እና ብርሃናማውን ሰላም እውን ለማድረግ ዘርፈ ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

ጥረቶቹም በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ላይ በተደረሰ የሰላም ስምምነት ወደ ፍሬነት የተሸጋገሩ ሲሆን፤ ይሄንን ፍሬ ዜጎች እንዲያጣጥሙት ለማድረግም ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚህ ረገድ ቀዳሚው ተግባር ቁጭ ብሎ መነጋገር እና ከጦርነት ወደ ሰላም በሚያሸጋግሩ ጉዳዮች ላይ መልካም ውይይትን ማድረግ ነበር፡፡ በዚህም በመንግስት እና በሕወሓት አመራሮች እንዲሁም የጦር አዛዦች መካከል የተደረጉ ንግግሮች ዜጎች ከሰላም ስምምነቱ ፍሬ ተቋዳሽ እንዲሆኑ ያስቻለ ነበር፡፡

ይሄንን የበለጠ ከማጠናከር አኳያም በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተመራ እና የክልል ርዕሳነ መስተዳደሮችን እንዲሁም የከተማ አስተዳደር ከንቲባዎችንና ሚኒስትሮችን የያዘ ልዑክ ወደ መቐሌ ተጉዞ ዜጎችን ከሰላም ስምምነቱ የበለጠ ተጠቃሚ ማድረግ በሚቻልበት ሂደት ላይ መክሯል፡፡ ይሄም ጦርነትን ወደ ሰላም መቀየር ብቻ ሳይሆን፤ ሰላምን የበለጠ ማጽናት የሚቻልበትን ሕዝባዊ አቅም የፈጠረ ነበር፡፡

ይሄም ሰላም እንደ ፀብ ምክንያት የማይፈልግ፣ ይልቁንም ስለ ሕዝብ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ከሚጨነቅ ስብዕና እንደሚመነጭ፤ ሰላም ግጭትን ለመፍጠር እንደሚደረግ ዝግጅት የተለየ ጊዜና ሁኔታንም እንደማይፈልግ፤ ይልቁንም ሰላም የሚፈልገው ቀና ሃሳብ እና የይቅርታ ልብ መሆኑን ያሳየ ነው፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ ለኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ሰላም እውን መሆን የተጉና የለፉ አካላትን የማመስገኛ መድረክ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት “ፀብ አቁሞ ሰላም ለመፍጠር በቂ ያልሆነ ምክንያት፤ ትክክለኛ ያልሆነ ጊዜም የለም፤” ሲሉ የተናገሩትም ይሄንኑ የሚያረጋገጥ ሃቅ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ መልዕክታቸው ሰላምን ማጽናት ትልቅ ጀግንነት፣ የልብን ቆራጥነት እና ለሕዝብ መሰጠትን የሚጠይቅ ስለመሆኑ አስገንዝበውም ነበር፡፡ በወቅቱም ሦስት ዓመት ከመዋጋት 20 ዓመት መነጋገርና መወያየት እንደሚገባ፤ ኢትዮጵያውያንም በውይይትና በምክክር ችግሮቻችንን መፍታት መለማመድ እንዳለብን፤ ከምክር ይልቅ መከራ የሚመክረን እንዳንሆንም አስገንዝበው ነበር፡፡ በመነጋገርና በመወያየት በይቅርታና እርቅ ከተበላሸው ትናንት ይልቅ የተዋበ ነገን ለመፍጠር መስራት እንደሚገባም አሳስበው ነበር፡፡

ከዚህ አኳያ በጦርነቱ ከፍ ያለ ጉዳት የተከሰተባቸው አካባቢዎች (ትግራይ፣ አማራ እና አፋር ክልሎች) አብነት ሆነው እንዲገለጡም አስገንዝበው ነበር፡፡ ለአብነትም፣ የትግራይ ክልል ጊዚያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳደር አቶ ጌታቸው ረዳ እና የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ወደ አማራ ክልል እና ወደ ትግራይ ክልል ተጉዘው ተቃቅፈው ይቅርታን፤ ተቀራርበውም መወያየትን በመግለጽ ለህዝቦች የሰላምን ልዕልና እንዲገልጡ ነግረውም ነበር፡፡

ይሄን መነሻ በማድረግም ከሰሞኑ የትግራይ ክልል ጊዚያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳደር አቶ ጌታቸው ረዳ ሰሞኑን ባህርዳር ተገኝተው ይሄንኑ አሳይተዋል፡፡ በቀጣይም የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ይሄንኑ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፡፡ ይሄን መሰሉ ወንድማማችነትን እና ቁጭ ብሎ መነጋገርን መርሁ ያደረገ የሰላም ሂደት ደግሞ፤ በአመራሮች ጥረት እና በሕዝቦች የጸና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ መጓዙ መልካም ቢሆንም፤ ሂደቱ በሁሉም የፖለቲካ ልሂቃን እና ፖለቲከኞች ሊታገዝ ካልቻለ በሚፈለገው ልክ ሊጓዝም ሆነ ውጤታማ ሊሆንም አይችልም፡፡

በመሆኑም በየደረጃው ያለው አመራር፣ የሕዝብ እንደራሴ፣ እና ሕዝቡም የቀደመ ሰላምና አንድነቱን፣ ወንድማማችነትና አብሮነቱን ለመመለስ ሊሰራ ያስፈልጋል፡፡ በሁሉም ወገን ያሉ አንዳንድ የፖለቲካ ልሂቃንና ፖለቲከኞችም ዳር ቆሞ ከመተቸት፣ ሂደቱን ከማጠልሸትና ወደኋላ ከመጎተት እሳቤ መውጣትም ይኖርባቸዋል፡፡ የሆነውን እያሰቡ ከመቆዘምና ቂም ቋጥሮ ከመኖር ተወያይቶ በፍቅርና ይቅርታ ተሻግሮ የወደፊት ብልጽግናን መተለምና ለዚሁ በጋራ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ እንዲሆንም የሰላሙን ሃሳብና ጉዞ እንዲጸና ሁሉም ሊደግፈው ይገባል!


አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የምስራቅ አፍሪካ ጂኦ ፖለቲካ እና የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ

መላኩ ኤሮሴ

የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ከትናንት እስከ ዛሬ የቀጣናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ኃያላን አገራት ተፅዕኖ ሳይላቀቅ ኖሯል፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት በፍጥነት እየተለወጠ ያለውን ዓለም አቀፍ ስርዓት ተከትሎ የቀጣናው ጂኦ ፖለቲክስ ላይ ተጨባጭ ለውጦች እየታዩ ነው፡፡ እንደ ሰውዲ አረቢያ እና ኢራን የመሳሰሉ የመካከለኛ ምስራቅ ቀጣናዊ ተጽዕኖ ፈጣሪ አገራት፣ እንደ ዩ.ኤስ.ኤ፣ ሩሲያ፣ ቻይና፣ አውሮፓ ህብረት ያሉ ዓለም አቀፍ ተዋናዮችም በአካባቢው ያላቸውን ተፅዕኖ ለማሳደግ፣ የኃይል የበላይነትን ለማረጋገጥ እና የአካባቢውን ሀብት ለመቀራመት የሚያደርጉት ጥረት ከመቼውም ጊዜ በላይ በተጠናከረ መልኩ ቀጥሏል፡፡

ለዚህም ነው ቀይ ባህር እና ባብኤል ማንደብ አካባቢ ከዚህ ቀደም የጦር ሰፈር ከገነቡት አገራት በተጨማሪ አዳዲስ አገራትም የጦር ሰፈራቸውን ለመገንባት ደፋ ቀና እያሉ ያሉት፡፡ ይህ ቀጣና ኑክሌይርን የታጠቁ ሁሉም ኃያላን አገራት የጦር ሰፈራቸውን የሚገነቡበት አካባቢ ከሆነ ሰነባብቷል፡፡ አብዛኞቹ የኑክሌር ኃይል የታጠቁ አገራት የጦር ሰፈር በዚህ አካባቢ ገንብተዋል፡፡ በቅርቡ ሩሲያም ከሱዳን ጋር በመነጋገር በቀይ ባህር ላይ የጦር ሰፈር ለመገንባት እንቅስቃሴ መጀመሯ ተሰምቷል፡፡

እነዚህ አካባቢዎች ለኢትዮጵያ ካላቸው ቅርበት አንጻር በአካባቢዎቹ የሚካሄዱ ኩነቶች ለኢትዮጵያ የራሱ ትርጉም አለው፡፡ በአካባቢው አገራት የሚሆኑ ነገሮች ኢትዮጵያ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የራሱ ጫና የሚያስከትል ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ከኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ የሚጠበቁ ነገሮች አሉ፡፡ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምን ያስቀደመ መሆን አለበት፡፡ ለዚህም አገራዊ ክብርን ማስጠበቅ፣ ጠላትን መቀነስ እና ወዳጅ ማብዛት አስፈላጊ ነው፡፡

የቀጣናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተፅዕኖ ፈጣሪ አገራት እሽቅድድም ሜዳ የሆነው ምስራቅ አፍሪካ በተለይም አፍሪካ ቀንድ ጉዳይ ሁል ጊዜም ከኢትዮጵያ ከዲፕሎማሲ አጀንዳዎቿ መካከል ዋነኛው አድርጋ ልትይዘው ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ የቀጣናውም ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት አስገብታ መንቀሳቀስ ያለባት ለራሷ ብሄራዊ ጥቅም እና ለቀጣናው ሰላምና መረጋጋት ስትል ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተሰሩ መልካም ጅምር ስራዎች ቢኖሩም አሁንም ሊሰሩ የሚገቡ በርካታ ስራዎች አሉ፡፡

ለምሳሌ፣ በጎረቤት አገሮች ሰላም ለማውረድ ኢትዮጵያ ጥረት እና የጎረቤት አገራትን የጸጥታ ተቋማት ለማጠናከር ጥረት ስታደርግ ቆይታለች፡፡ በሶማሊያ፣ በደቡብ ሱዳን እንዲሁም በሱዳን ሰላም ለማምጣት ኢትዮጵያ የአንበሳውን ድርሻ ስትወጣ ቆይታለች፡፡ በዚህም በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ አድናቆት ተችሯታል፡፡ አሁንም ጥረት እያደረገች ነው፡፡ እነዚህ ጥረቶች ለኢትዮጵያ ፋይዳው ከፍ ያለ ነው፡፡

የኢትዮጵያን ጥቅም የማይጎዳ እና ኢትዮጵያን የመልማት ፍላጎት የማያደናቅፍ እስከሆነ ድረስ ከየትኛውም አገር ጋር መስራት ያስፈልጋል፡፡ ከምዕራቡ ጎራ ሆነ ከምስራቁ ጎራ አገራት ጋር ብሄራዊ ጥቅምን መሰረት ያደረገ ግንኙነት ማድረግ አለባት፡፡ የአገራቱ የፖለቲካ ርዕዮት ጉዳይ ኢትዮጵያን ሊያስጨንቃት አይገባም፡፡ ኢትዮጵያ የየትኛውም ርዕዮት እስረኛ መሆን የለባትም፡፡

ዋናው ጉዳይ የአገር ውስጥ ጥቅም በኃያላኑ እንዳይጠመዘዝ ጥንቃቄ ማድረጉ ላይ ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የሚቀርቡ ብድሮች እና እርዳታዎች እንደ ቅድመ ሁኔታ በመጠቀም አደጋ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ይሻል፡፡ በተለይም ኃያላን አገራት እና የፋይናንስ ተቋማት የሚያቀርቧቸው ምክረ ሀሳቦች በጥርጣሬ መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ1980ዎቹ እና ዘጠናዎቹ የብሪተን ውድስ ተቋማት (የዓለም ባንክ እና የዓለም የገንዘብ ድርጅት ( አይ ኤም ኤፍ)) ስትራክቸራል አጀስትመንት በሚል ሰበብ በበርካታ የአፍሪካ አገራት ላይ ያደረሱት አይነት ቀውስ እንዳይከሰት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይሻል፡፡

ከምንም በላይ ግን ዲፕሎማሲው የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው የውስጥ አንድነትን ማጠናከር ሲቻል ነው፡፡ የውስጥ አንድነትን ማጠናከር ካልተቻለ ለውጫዊ ጥቃት የመጋለጥ እድል ይሰፋል፡፡

**ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ ቀንድ ኃያል አገር ናት፡፡ ይህ በተለያዩ ምክንያቶች የመጣ ኃይል ነው፡፡ ውስጣዊ አንድነትን ለማጠናከር እና ኢኮኖሚውን ለማንሰራራት የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክሮ ከቀጠለ ቀጣናዊ ኃያልነቷን ወደ አህጉራዊ ኃያልነት የማታሳድግበት ምክንያት የለም**

በመሆኑም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ልዩነቶችን በንግግር በመፍታት አገራዊ አንድነትን ለማጠናከር የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡

በዚህ ረገድ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ለሁለት ዓመታት የዘለቀውን ደም አፋሳሽ ጦርነት በንግግር እና በውይይት ለማስቆም የተሄደበት ርቀት የሚያስደስት ነው፡፡ የሰሜኑ ችግር ከተፈታ በኋላ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያለውን ችግርም በንግግር እና በድርድር ለመፍታት የተጀመሩ ጥረቶች ውጤት እስኪያመጡ መቀጠል አለበት፡፡ ብሄራዊ የምክክር ኮሚሽን የጀመረውን አገራዊ ምክክር ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ውስጣዊ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት እየተደረገ ያለው ጥረት የዲፕሎማሲ ስራው ፍሬ እንዲያፈራ የሚያበረክተው ሚና የላቀ ነው፡፡

ውስጣዊ አንድነትን ከማጠናከር ጎን ለጎን ኢኮኖሚያዊ ስኬት ለዲፕሎማሲው መቃናት ፋይዳው ከፍ ያለ ነው፡፡ ጠንካራ ኢኮኖሚ የሌለው አገር እሳት የላሱ ዲፕሎማቶችን በመላው አገር ቢያሰማራ የሚፈልገውን ለማሳካት ሊቸገር ይችላል፡፡ በኢኮኖሚ ጡንቻ ያልተደገፈ ዲፕሎማሲ ከንቱ ድካም ነው፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ በኢኮኖሚው ረገድ ባለፉት ጊዜያት ሲታይ የነበረውን በጎ ጅምሮችን ዳግም ለማሳካት መንቀሳቀስ ይገባል፡፡ በተለይም በግብርና፣ በማዕድን፣ በቱሪዝም እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች እድገት ለማስመዝገብ የተጀመሩ ስራዎች ሊቀጥሉ ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ ቀንድ ኃያል አገር ናት፡፡ ይህ በተለያዩ ምክንያቶች የመጣ ኃይል ነው፡፡ ውስጣዊ አንድነትን ለማጠናከር እና ኢኮኖሚውን ለማንሰራራት የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክሮ ከቀጠለ ቀጣናዊ ኃያልነቷን ወደ አህጉራዊ ኃያልነት የማታሳድግበት ምክንያት የለም፡፡ ከአፍሪካ አህጉር አልፎ መካከለኛ አቅም ያላት ኃይል፤ እንዲሁም በቀይ ባህር አከባቢ ተጽዕኖ ፈጣሪ ኃይል የመሆን እድሏ ከፍ ያለ ነው፡፡

ውስጣዊ አንድነት ከሌለና ኢኮኖሚ አቅም ከሌለ በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ፊት ያላት ተሰሚነት አነስተኛ ይሆናል፡፡ ጠንካራ ውስጣዊ አንድነት ከሌለ የአገርን ጥቅም ከማስቀደም ይልቅ ኃያላንን ላለማስቆጣት መጨነቅ ይመጣል፡፡ የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም ሳይሆን የኃያላን ፍላጎት አስፈጻሚ እንሆናለን፡፡ በመሆኑም ከምንም በላይ ውስጣዊ አንድነትን ለማጠናከር እና ኢኮኖሚያዊ አቅምን ለማፈርጠም በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡ ይህ ሲሆን ኢትዮጵያ በቀጣናው ያላትን ተጽዕኖና ተደማጭነት ማግኘት፤ ዲፕሎማሲዋንም ማጠናከር ትችላለች፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# በእኛነት የተቃኘ ብሔራዊ ምክክር ለብሔራዊ ተግባቦት

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለተሻለ ሀገራዊ ተግባቦትን ለመፍጠር በብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን በኩል እንቅስቃሴ እያደረገች እንደሆነ ይታወቃል። ይሄም እንቅስቃሴ በተመረጡ ባለሙያዎች ለዓመታት ቅድመ ዝግጅት ተደርጎበት ወደሥራ ሊገባ የተሳታፊ ምልመላ እና አጀንዳ ልየታ ደረጃ ላይ መድረሱ በመግለጫም እየተነገረ፤ በተግባርም እየታየ ይገኛል።

በዚህ ረገድ እንደሀገር የተደቀኑብንን ማናቸውንም ዓይነት ፈተናዎች በጦርነት ሳይሆን በሰላም፣ በጥላቻ ሳይሆን በይቅርታ ለመሻገር እየተደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ ነው። እንዲህ አይነቱ ዘመንኛ እሳቤ ከትላንት ወደ ዛሬ መጥተው እድፍ ያለበሱንን የፖለቲካ ትኩሳቶች በመሻር አንድነትን እንደሚሰጠን እሙን ነው።

ምክንያቱም እኛ ዛሬ ላይ አንድ እግራችን ትላንት ላይ አንዱን ደግሞ ዛሬ ላይ ቆሞ በመንታ ልብ ጥንድ ሀሳቦችን ስንካድም ከሚገባን ፈተኝነት ተቆራርጠናል። ወዴት እንደምንሄድ መንገድ ጠፍቶን አሻጋሪ ስንፈልግ የመቆየታችን ጉዳይም መገለጫችን ነበር። አዲስ መንገድ መሥራት አቅቶን በተራመድነው መንገድ ላይ ደጋግመን ስንመላለስም ዓመታት ተቆጥረዋል።

እናም እነዛ ከመሄድ ባለፈ፣ ከድካም ባለፈ ብርታት ያልሰጡን ጎዳናዎች ዛሬ ላይ በምክክርና በውይይት ተሸረው "ሎጥ" የሄደባቸው የፀጋ ጎዳናዎች እንዲሆኑ ተረት ወለድ ትርክቶቻችንን ሽረን በእርቅና በመተቃቀፍ ዳግም ልንሄድባቸው ጥርጊያ ጀምረናል። ለአዲስ ሀሳቦች ቅድሚያ ሰጥተን ያለፈው የቁርሾ ጊዜ ባለፈ አስተሳሰብ ስር እንደነበር አምነን በመቀበል አዲሱን የእርቅ መንገድ በአዲስ ሀሳብ መጀመር መቻልም፣ ማስቻልም የብሔራዊ ምክክር አጀንዳችን ተቀዳሚ ወግ ነው።

በዚህ ረገድ ብዙ ተራምደን ወደረፍት የሚወስድ የማርያም መንገድ ልናገኝ ልባችንን ከጥላቻ ስላላጸዳን ነው። ማናችሁ? ስንባል ኢትዮጵያውያን ነን እንላለን፤ በማንነታችን ውስጥ ግን ከአባቶቻችን የወረስነው የአንድነትና የፍቅር እውነት ምን ያህል አብሮን አለ የሚለውን ግን ለሁላችንም ጥያቄ ሆኖ ይቆይ። ምክንያቱም ይሄን መሰሉ ኢትዮጵያዊ ሆኖ በመለያየት ውስጥ መቆም ነው የደስታ መንገዳችንን የሰወረብን።

ኢትዮጵያዊነት ውስጥ የእኔ ብቻነት የለም። ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ዘረኝነት የለም። ለምን ቢባል፣ ኢትዮጵያዊነት መነሻው በብዝኃነት ውስጥ ደምቆ የሚገለጽ አንድነት ነው፤ መድረሻውም እኛነት ነው። የአባቶቻችን ሀገር የመፍጠር ዓላማ ከዛም ባለፈ ሀገር የማጽናት እውነት በዚህ አንድነትን መሠረት ባደረገ የመነሻና የመድረሻ እሳቤ ውስጥ የጸና ነው።

እኛ የዛኛው ትውልድ በአንድነቱ ሀገር የሠራው የአባቶቻችን መልክ ነን። በዚህ መልክ ውስጥ የብሔር ሽኩቻ፣ የእኔነት ውዳሴ የለም። ይሄ መልክ በኢትዮጵያዊነት የቆነጀ፣ በኅብረብሔራዊነት ያጌጠ የብዙነት ቀለም ነው። ከብዙነት ውስጥ እኔ ብለን ራሳችንን ብቻ ስናወድስ ኢትዮጵያዊነት የተሠራበትን የጋራ እውነት እያላላን ነው።

ዛሬ ላይ ጠብቆ ተገምዶ ግን ደግሞ የላላው የአባቶቻችን እውነት ከብዙ ማንነት ውስጥ ራሳችንን ብቻ የማድመቃችን፣ የማወደሳችን፣ የመነጠላችን፣ የማሞካሸታችን ጣጣ ነው። በብሔር ስም ተቧድነን፣ ከትላንት አብራክ ውስጥ ነውር እየመዘዝን የምንጠላላው ጥላቻ፣ የምንቀያየመው ቅያሚ የጸነሰው ግፍ ጽንስ ነው።

ስለሆነም ብዙ ተጉዘን ካልደረስንበት የእረፍታችን ምኩራብ ለመድረስ በኅብር ደምቀን በአንድነት የምንራመድበት የማርያም መንገድ ያስፈልገናል። ምክንያቱም የድህነት አቀበት በመያያዝ የሚታለፍ ነው። ሳይያያዝና በአብሮነት ሳይቆም ታሪኩን የለወጠ ሀገርና ሕዝብ የለም።

የሠለጠኑትን አገራት የሥልጣኔ ታሪክ ብናጠና የሀገር ፍቅር ስሜታቸው ከእኛነት መንፈስ ውስጥ እንደፈለቀ እንደርስበታለን። በተቃራኒው ብዙ ሕዝብ ይዘው፣ ብዙ የተማረ የሰው ኃይል አቅፈው፣ በወጣትና በተፈጥሮ ሃብት ደምቀው ግን ደግሞ ከምኞት ባለፈ ከነበሩበት ፈቀቅ ያላሉ ሀገራት ጥቂቶች አይደሉም። የእኚህን ሁለት ሀገራት የአስተሳሰብ አድማስ ብንፈትሽ እኔነትና እኛነት ሆኖ እናገኘዋለን።

> **በኢትዮጵያ** ስዕል ውስጥ የሁላችንም ብሩሽ አለ። ኢትዮጵያን የሳላት የሁላችን ሀሳብ፣ የሁላችን ሥርዓት ነው። ከዚህ ውስጥ አንዱ ቢጎድል ደብዛዛዋን ኢትዮጵያ ነው የምናገኘው። የብኩርና ግፊያችን ማናችንንም ፈተኛ አያደርግም። ኢትዮጵያን ከመጣል፣ አንድነታችንን ከመነቅነቅ ባለፈ የሚጨምርልንም የኃይል አቅም የለም

እኔ ብለን እስካልተነሳን ድረስ መለያየትን መፍጠር አይቻለንም። እኔነት ብዙዎች ለብቻቸው ኖረው፣ ለብቻቸው አስበው፣ ለብቻቸው የሚሞቱበት መቃብር ነው። ታላቁ ሩሲያዊ ደራሲ ፊዮዶር ዶስቶፍስኪ ይሄን የእኔነት እሳቤ ተንተርሶ እንዲህ ብሎ ነበር ‹እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ ሲዖል ማለት ሌሎችን አለማፍቀር የሚፈጥረው የሕመም ስሜት ነው› ሲል ራስን ከሌሎች መነጠልን ክፉ ከሆነችው ሲዖል ጋር አዛምዶታል።

ብዙ ሆነን ግን በአንድነት ሆነን ከትላንት ወደ ዛሬ የመጣነው አንድ ላይ ሆነን ስለቆምን ነው። እናም ዛሬ ላይ ለገጠመን ስብራት እድሳት ያስፈልገናል። ዛሬ ከትላንቱ ሌላ ቀን ነው። ዓለም በሥልጣኔው ሩቅ በደረሰበት በዚህ ሥልጡን ዘመን ላይ በትላንት ፖለቲካ፣ በትላንት ጥፋት፣ በትላንት ትርክት ዛሬን መኖር ከምንም የማይወዳደር ጥፋት ነው።

እኔነት ከነውርና ስር ከሰደደ ራስወዳድነት ባለፈ ለትውልዱ መጥፎ የሚያስተምር፣ በራስና በሀገር ላይ መጨከን ነው። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በእኔነት ስሜት ውስጥ ስንገባ በራሳችን ላይ ጨክነናል ማለት ነው። በዚህ ስሜት ውስጥ ሆነን በምናስበው ሀሳብ፣ በምናራምደው እምነት እየጎዳን ያለነው ራሳችንን ነው። የሚጠቅመን በጋራ ሀሳብ የጋራ ጥቅማችንን መፍጠር ነው።

ሀሳቦቻችን ወደጥፋት ከማምራታቸው በፊት የሚገራ፣ የሚያቀና እውቀት ያስፈልገናል። ያልገባን እንዲገባን ከፈለግን የገቡን የስህተት እውነቶች መሻር አለባቸው። አሁን የሚያስፈልገን ያልገባን እንዲገባን ነው። ከገቡን ይልቅ ያልገቡን እንደሚበጁን ገብቶናል፤ ለዚህ ደግሞ ገባን ባሉ ግን ባልገባቸው "ፖለቲከኞች" የደረሱብንን ጥፋቶች ማየቱ በቂ ነው።

እረፍታችን ያለው ባልገቡን እውነቶች ውስጥ ነው። ያልገቡን እውነቶች እንዲገቡን ራሳችንን በኢትዮጵያዊነት ሥነምግባር ማነጽና የአባቶቻችንን ሀገር የመፍጠር እውነት መከተል አለብን። ያልገቡን እንዲገቡን ሰላምን በጦርነት ከማምጣት እሳቤ ወጥተን ከጦርነት በፊት ሰላም፣ ከጥላቻ በፊት ፍቅርን የሚል አዲስ እውቀት ሊዋሐደን ይገባል።

ያልገባን አንድ እውነት ቢኖር ኢትዮጵያን በአንድ ብሔር ብቻ የመጥራት አባዜ ነው። ኢትዮጵያ በአንድ ብሔር የበላይነት ብቻ አትለወጥም። ሀገር ማለት ብዙነት ነው። ሀገር ማለት የብዙ ሀሳቦች፣ የብዙ ስርጭቶች፣ የብዙ ባሕልና ወጎች ጥርቅም ነው።

በኢትዮጵያ ስዕል ውስጥ የሁላችንም ብሩሽ አለ። ኢትዮጵያን የሳላት የሁላችን ሀሳብ፣ የሁላችን ሥርዓት ነው። ከዚህ ውስጥ አንዱ ቢጎድል ደብዛዛዋን ኢትዮጵያ ነው የምናገኘው። የብኩርና ግፊያችን ማናችንንም ፈተኛ አያደርግም። ኢትዮጵያን ከመጣል፣ አንድነታችንን ከመነቅነቅ ባለፈ የሚጨምርልንም የኃይል አቅም የለም።

እናም ወዳልገቡን እውነቶች እንማትር። ፖለቲካው ያስተማረንን፣ ሳይገባቸው ገባን የሚሉ ፖለቲከኞች የሰጡንን የእኔነት ሀሳብ ሽረን የአባቶቻችንን እውነት እንከተል። ይሄ ደግሞ ለእውነትና ለእርቅ ከተጠቀምነው ብሔራዊ ምክክር መንገድ የሚሰጠን ነው። በጥላቻ የዘጋነውን፣ በራስወዳድነት የራቅነውን የእረፍት መንገድ የሚተልምልን ነው።

ልጅ ሆነን ስንጫወት በሁላችንም ዘንድ የሚዘወተር አንድ አባባል አለ ‹የማርያም መንገድ ስጠኝ› የሚል። የማርያም መንገድ ወደ እረፍት መሄጃ፣ የሀሳብና የምኞት መዳረሻ ነው። ይሄ መንገድ በፍቅር የሚተለም፣ በይቅርታና በመቻቻል የሚጠረግ የአብሮነት ሰርጥ ነው። መንገዶቻችንን የዘጋነው ራሳችን ነን። የአባቶቻችንን የእውነትና የሐቅ መንገድ ስተን ፖለቲከኞች በሰጡን የእኔነት መንገድ ላይ የቆምነው ባልገባን እውቀት ነው።

መንገድ ያስፈልገናል። ይሄ መንገድ ግን ወደ ሰላም መሄጃ፣ ወደ አንድነት ማስተዋያ መንገድ ነው። ይሄ መንገድ ወደእርቅ፣ ወደፍቅር የሚወስድ ነው። ብሔራዊ ምክክር ከያዛቸው ዓላማና እቅዶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ደግሞ ይሄንን እውን ማድረግ ነው፤ በብሔራዊ ምክክር ብሔራዊ ተግባቦትን በመፍጠር ይሄን አይነቱን መንገድ መክፈት ነው።

የምክክር ጽንሰ ሀሳብ በየትኛውም ሀገርና ባሕል ውስጥ አንድ አይነት ነው፤ እርሱም መግባባትን መፍጠር ነው። ዓለም ላይ በእንዲህ አይነቱ የምክክር ዘዴ ሀገራቸውን ከተጣመመችበት ያቃኑ ብዙ ናቸው። አይደለም ሰው ከሰው፣ አይደለም ፖለቲከኛ ከፖለቲከኛ ቀርቶ በአንድ ልብና አዕምሮ እየተመራ እንኳን እግር ከእግርም ይጋጫል።

ትልቁ እና ሊሰመርበት የሚገባው ነገር ያደናቀፈን እንቅፋት መልሶ እንዳያደናቅፈን ከመንገዳችን ላይ ገለል ማድረግ ነው። የእኛ ችግር እንቅፋቱን ከመንገዳችን ላይ ሳናነሳ አንድ ጊዜ ባደናቀፈን እንቅፋት ደጋግመን መደናቀፋችን ነው። ለጦርነት እና ለመለያየት እየዳረጉን ያሉ ችግሮችን መለስ ብለን ብናይ አንድ አይነት ሆነው እናገኛቸዋለን።

በአንድ አይነት እንቅፋት፣ በአንድ አይነት መንገድ ላይ ደግመን ደጋግመን የምንወድቅ ነን። ከትላንት እስከዛሬ ፖለቲካችን መደናቀፊያችን ነው። ከድሮ እስከዘንድሮ የማንነት ጉዳይ መነታረኪያችን ነው። መንገዳችንን ማጥራት አለብን። ስናልፍና ስናገድም በአንድ አይነት መንገድ ላይ በአንድ አይነት እንቅፋት መመታታችን እንዲቀር በእንቅፋቶቻችን ላይ ለውይይት መቀመጥ መፍትሔ የሚሰጠን መላ ነው።

ፖለቲካችን እንዳያደናቅፈን፣ ያልኖርነው ትላንትና እንዳያቀያይመን በእውቀትና በሥርዓት የተመራ የተሐድሶ ንቅናቄ ያሻናል። ንቅናቄው የሚጀምረው በአዲስ ሀሳብ ነው። አዲስ ሀሳብ የአዲስ መላ፣ የአዲስ መፍትሔ አብራክ ነው። እስከዛሬ ባልታደሰ ሀሳብ ለውይይት ተቀምጠን ለውጥ ሳናመጣ ቀርተናል።

የምንወያየው ለለውጥ ነው። ያደናቀፉን እንቅፋቶች ዳግም እንዳይጥሉን እንዴት ከመንገዳችን ላይ ገለል እናድርጋቸው የሚል ምክረ ሀሳብን ለማዋጣት ነው። በተዋጣና በታመነበት ሕዝባዊ ተሳትፎ በእንቅፋቶቻችን ላይ ስንወያይ ብቻ ነው መንገዳችንን ከጋሬጣ የምንጠብቀው።

ለችግሮቻችን የመፍትሔ ሀሳብ ከሌለን ያ መንገድ፣ ያ ፖለቲካ፣ ያ እንቅፋት እንዲያደናቅፈን ፈቅደናል እንደማለት ነው። አሁን ላለችው ኢትዮጵያና አሁን ላለው ሀገራዊ ተግዳሮት ከችግሮቻችን የሚበልጥ የመፍትሔ ሀሳብ ነው የሚያስፈልገን። ከችግሮቻችን በሚበልጥ የመፍትሔ ሀሳብ ነው ፖለቲካችንም ሆነ ሌሎች ነውሮቻችን የሚታከሙት።

እስከዛሬ ተወያይተን መፍትሔ ያላመጣነው በችግሮቻችን ስለተበለጥን ነው። በችግሮቻችን በመበለጣችንም በአንድ አይነት መንገድ ላይ እየተጓዝን በአንድ አይነት እንቅፋት እየተመታን ደጋግመን ወድቀናል። በመሆኑም ከችግሮቻችን የላቀ ሁሉን አቀፍ የለውጥና የተሐድሶ ተራማጅ እሳቤ ያስፈልገናል።

ብሔራዊ ምክክር ደግሞ ብሔራዊ ተሐድሶን የሚሰጠን የአዲስ ለውጥ ንቅናቄ ነው። እንቅፋቶቻችን በዛ መድረክ ላይ በሀሳብ የበላይነት ተኮርኩመው ተነቃንቀው መውደቅ አለባቸው። ከዛም ከዚም የመጡ አሁናዊና ድሯዊ ነውጥ ፈጣሪ ተግዳሮቶች እንደ ልብስ በሀሳብ ሳሙና ታጥበው መጥራት አለባቸው።

ሀሳባችን ነውራችንን ካላጠራልን በምንም አንጠራም። ፍቅራችን እድፋችንን ካላጸዳልን በምንም አንጸዳም። እንደሕዝብ ለምክክር ስንቀመጥ እንዴትም፣ ከየትም ይምጡ በችግሮቻችን ላይ የበላይ ለመሆን ነው። ከፊታችን ያለው ሀገራዊ ምክክር ትኩሳቶቻችን የሚሽሩበት የብዙዎቻችን የትንሣኤ ፀሐይ የሚወጣበት የተስፋ ምሥራቅ ነው።

ብሔራዊ ምክክር ለብሔራዊ ተግባቦት እንደ አንድ የዋርካ ስር ነው። ዛፍ በስሩ እንደሚጸና ሀገርም በሀሳብ ነው የምትጸናው። ሀሳብ ግን አይነት አለው። ሀገር የማጽናቱን ያክል ሀገር የሚያፈርሱ ሀሳቦች አሉ። ዓላማችን ሀገር ማጽናት፣ ብሔራዊ አንድነትን ማምጣት እስከሆነ ድረስ በስሮቹ እንደጸናው ዛፍ በዜጎቿ ሀሳብ የጸናች ሀገር ታስፈልገናለች።

ዛፍ ስር ከሌለው ግንድና ቅርንጫፉ፣ አበባና ፍሬው ምንም ነው። ልክ እንደዚህ ሁሉ ሀገር አስታራቂና አንቂ፣ አስማሚ ሀሳብ ከሌላት አበባና ፍሬ፣ ቅርንጫፍና ግንድ እንደሌለው የይስሙላ ዛፍ ናት። የዚህ ውጤቱ ደግሞ በፖለቲካ እንቅፋት መደነቃቀፍ፣ ባልተኖረ ትላንትና ባልመጣ ነገ መባላት የመሳሰሉት ነውሮች ይጠቀሳሉ።

እንደ ሀገር ወደራቀ ነገ ለመዝለቅ፣ አብሮ እንደመጣ፣ አብሮ እንደኖረ፣ አብሮ እንደተዋለደ ሕዝብ የጋራ ሀገርና የጋራ ታሪክ ለመሰነድ በተረት ሳይሆን በእውነት፣ በብሔር ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት የሚያምን ፖለቲካና ፖለቲከኛ፣ ዜጋና ትውልድ፣ ምሑርና አስተማሪ፣ አንቂና አስታራቂ ያሻናል።

በአብሮነትን በሚያጠናክር የእኛነት መንፈስ የተቃኘ ብሔራዊ ምክክር ለብሔራዊ ተግባቦት ወሳኝ መሆኑን ስገልጽ፣ ይሄን በመሰለው ምክንያት ላይ ቆሜ ነው። ኢትዮጵያን የሚያሻግር፣ የሚታደግ፣ የሚደግፍ፣ የሚለውጥ ሀሳብ ከብሔራዊ ምክክር ተሳታፊዎች እንጠብቃለን። ትውልዱ አንድነቱን ጠብቆ የጋራ ሀገሩን በጋራ እንዲያለማ አባቶቹን የሚያስታውስ ዝክረ ዓድዋን የመሰለ የአንድነት ዓውድ ያስፈልገዋል። እንዲህ በመሰለው መንገድ ላይ ስንራመድ ብቻ ነው ትላንት ያደሙን እንቅፋቶቻችን ዛሬ ላይ እንዳይደግሙን የምናደርገው። ለዛሬው አበቃሁ፤ ሰላም!

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የተፈጠሩ ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ወቅቱ የህዝቡን ችግር መፍታት የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችና የፈጠራ ሀሳቦች እየወጡ ያሉበት ነው:: ችግሮችን መነሻ በማድረግ የማህበረሰቡን ችግር ለማቃለል በሚደረገው አገራዊ ጥረት አገር በቀል እውቀቶችን ተጠቅመው ፈጠራዎችና የፈጠራ ሀሳቦችን ለሚያቀርቡ የፈጠራ ባለሙያዎች እውቅና መስጠት፣ መደገፍና ማበረታታት አስፈላጊና ወሳኝ ነው::

በቅርቡም የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ያዘጋጀው 3ኛው የክህሎት ውድድር ለዚህ አንድ ማሳያ ነው:: ‹‹የክህሎት ልማት ከሥልጠና በላይ ነው›› በሚል መሪ ሃሳብ የተካሄደው 3ኛው የክህሎት ውድድር በርካታ ችግር ፈቺ የሆኑ የፈጠራ ውጤቶች ለእይታ ቀርበውበታል:: ይህም አገር በቀል እውቀቶች፣ የፈጠራ ሀሳቦችና የፈጠራ ቴክኖሎጂዎችን በማበረታታት ረገድ አበረታች ጅምር ነው::

በክህሎት፣ በቴክኖሎጂና በተግባራዊ ጥናትና ምርምር ዘርፍ በተካሄዱ ውድድሮችም ከሶስት መቶ በላይ ሰልጣኞች፣ አሰልጣኞችና ኢንተርፕራይዞች ተሳትፈዋል:: 113 የሚደርሱ ቴክኖሎጂዎች ለእይታ ቀርበው በብዙ ሺ በሚቆጠሩ ሰዎች መጎብኘታቸውንም ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያሳያል::

በክህሎት ውድድሩ ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የመጡ በርካታ የፈጠራ ባለሙያዎች ያላቸውን ፈጠራና ሀሳብ ለእይታ አቅርበዋል:: ለውድድር ይዘዋቸው ከቀረቡት የፈጠራ ሥራዎች መካከልም ጥቂቶቹን በመዳሰስ ከፈጠራ ባለሞያዎቹ ጋር ቆይታ አድርገናል::

የድሬዳዋ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ አሰልጣኝ መምህር ዮናስ ጥዑም ‹‹ፕሮሶፒስ ጁሊፍሎላ/Prosopis juliflora ››/ በተለምዶ ‹‹የፈረንጅ ብስኩት›› የተሰኘውን የአረም አይነት ለማጥፋት የሚያስችል የፈጠራ ቴክኖሎጂን ይዘው ቀርበዋል:: ይህ የአረም አይነት በአፋርና በሱማሌ ክልል በስፋት የሚገኝ ሲሆን፤ ልክ እንደ ዛፍ አይነት ነው:: አረሙ የከርሰ ምድርን ውሃ በስፋት ይመጣል፤ እሱ ባለበት አካባቢ ሌላ ተክል አይበቅልም፤ ሰፊ የእርሻ ቦታዎችን የሚይዝ ነው ሲሉ ይናገራሉ::

ይህ የፈጠራ ቴክኖሎጂ አረሙን ወደ ተለያዩ ነገሮች በመቀየር መልሶ አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ የሚያስችል ነው የሚሉት መምህር ዮናስ፤ የፈጠራ ቴክኖሎጂው ሁለት ነገሮችን በአንድ ላይ መስራት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ውጤት እንደሆነም ይገልጻሉ:: እሳቸው እንዳሉት፤ አዲሱ የፈጠራ ቴክኖሎጂ ማሽን ኦክስፋም (OXFAM) ከተሰኘው ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባባር የተሠራ ሲሆን፤ ለህብረተሰቡ ተላልፎ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል::

አረሙን ፍሬ ከብቶች ይመገቡታል:: ፍሬው በጣም ጠንካራ ስለሆነ ከብቶች ከበሉት በኋላ በሆዳቸው ውስጥ ስለማይፈጭ ተመልሶ በእበት/ እዳሪ/ መልኩ ይወገዳል:: ይህ ከከብቶቹ የተወገደው የአረም ፍሬ የከብቶቹ እበት እንደ ማዳበሪያ ስለሚሆንለት በደንብ እንዲበቅልና እንዲስፋፋ ያደርገዋል:: በአፋር ክልል በአረሙ ላይ የተካሄደው ጥናት እንደሚያመላክተው፤ አረሙ በዓመት ከ20 ሺ እስከ 50 ሺ ሄክታር ስፋት ያለውን መሬት የማዳረስ አቅም አለው::

በፈጠራ የተገኘው ማሽን ደግሞ አረሙን በተለያየ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ አረሙ እንዲጠፋ የሚያስችል መሆኑን የጠቀሱት መምህር ዮናስ፣ አረም የሆነው ዛፍ ከተቆረጠ በኋላ የሚጣል ምንም የሚጣል ነገር እንደሌለም ይናገራሉ::

ከዚህ የፈጠራ ማሽን አንዱ ማሽን ከሰሉን የሚፈጭ ሲሆን ሌላው ደግሞ ዘሩን የሚያመክን መሆኑን ይገልጻሉ:: የፈጠራ ማሽኑ አንደኛው ክፍል የአረሙን ግንድ ያከስላል፤ ከሰሉ ደግሞ ወደ ወፍጮ ማሽን እንዲገባ በማድረግ ይፈጫል:: ሁለተኛው የማሽን ክፍል ዘሩ ወይም ፍሬውን መፍጨት ያስችላል:: በማሽኑ የተፈጨውን ከሰል ከማጣበቂያ ጋር በመቀላቀል እንደ ብሪኬት አይነት አራት ማዕዘን ከሰል የሚያመርት ነው:: ይህ በተለምዶ ከምናውቀው የከሰል የጊዜ ቆይታ ይልቅ ብዙ ሰዓት መቆየት የሚችል ነው:: እንደ ባዮ ጋዝ ያለው የካርበን መጠን አነስተኛ ሲሆን፤ እሳቱም ልክ እንደባዮ ጋዝ አይነት እንደሆነ ይናገራሉ::



**የገብስ መፈተጊያ ማሽን**

ሌላኛው በማሽኑ የሚመረተው መኖው ነው፤ ማሽኑ ፍሬውን በመፍጨት ብቻውን ወይም ከበቆሎ ጋር በማደባለቅ ለከብቶች መኖነት እንዲውል ማድረግ የሚያስችል ነው:: ከአረሙ የሚዘጋጀው ይህ መኖ የወተት ምርት በከፍተኛ መጠን እንዲጨምር ያስችላል ያሉት መምህር ዮናስ፤ መኖውን ብቻ አልያም ከበቆሎ ጋር ቀላቅሎ በመፍጨት ማቅረብ ይችላል ይላሉ:: አረሙ ብዙ ያልታየና ገና ያልተነካ በመሆኑ ቴክኖሎጂው ሲስፋፋ ብዙ ሥራዎችን መሥራት ያስችላል ሲሉም ነው ያብራሩት::

እሳቸው እንደሚሉት፤ የአረሙ ዘር ስለመከነና ስለተፈጨ ከብቶች በመኖነት ሲመገቡት ምንም አይነት ጉዳት አያስከትልም:: መኖውን ከብቶቹ ሲመገቡት ከፍተኛ የወተት መጠን ማግኘት ይቻላል:: ይህም በአለማያ ዩኒቨርሲቲ በጥናት የተረጋገጠ ስለመሆኑ መምህር ዮናስ ተናግረዋል::

ይህ የፈጠራ ውጤት ሶማሌ ክልል ሲቲ ዞን ማርማርሳ ቀበሌ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች የቀረበ ሲሆን፤ 20 ለሚደርሱ ዜጎችም የሥራ እድል ፈጠሯል:: የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው ዜጎች መካከልም ስድስቱ ሴቶች ናቸው፤ ስለቴክኖሎጂው አጠቃቀም ስልጠና በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል::

ከዚህ በፊት አረሙን ዛፍ ቆርጦ ለማጥፋት ብዙ ሙከራ ቢደረግም፣ ዘሩ በጣም ጠንካራና ቶሎ የማይፈጭ በመሆኑ ማጥፋት ሳይቻል መቅረቱን ያነሱት መምህር ዮናስ፤ አሁን ላይ የተሰራው የፈጠራ ቴክኖሎጂ አረሙን መፍጭት የሚችል ነው ብለዋል:: ማሽኑ የአረሙን ዛፍ የተለያዩ አገልግሎቶች መስጠት እንዲችል አድርጎ በመጠቀም በአንዱ ማሽን ማቴሪያሎችን ብቻ በመቀያየር ሁለት ነገሮችን መፍጨት ይቻላል:: በአንድ ጊዜ እስከ አራት ሜትር ኪዩብ ወይም 1332 ኪሎ ግራም የሚፈጭ ሲሆን፤ ቴክኖሎጂው በኤሌክትሪክም በሶላር የሚሰራ ነው::

አረሙ በስፋት የሚገኙባቸው የሶማሌና አፋር ክልል አካባቢዎች ይሁኑ እንጂ በሌሎች ክልሎችም አለ:: ዛፉ እስከ 15 ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን እሾኩ ደግሞ ከሶስት እስከ አምስት ሳ.ሜ የሚረዝምና መርዛማ ነው:: ስሩም ከሶስት እስከ አምስት ሜትር ድረስ ጥልቀት አለው::

‹‹ይህንን ቴክኖሎጂ ለመስራት በተለይም ዘሩን (ፍሬውን) የሚፈጨውን ማሽን ለማግኘት ብዙ ሙከራዎች አድርገናል›› የሚሉት አሰልጣኙ፤ በውጤቱም ዘሩን ማምከን የሚያስችል ቴክኖሎጂ ማግኘት ችለናል ነው ያሉት:: አሁን ላይ ከአውሮፓ ህብረት የመጡ አካላት ቴክኖሎጂውን አይተው አስፋፍተው ለመስራት እንዲያስችል ጅግጅጋ፣ ድሬዳዋና ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በመሳተፍ እየሰሩበት ይገኛሉ::

ቴክኖሎጂውን ከቴክኒክና ሙያ ባሻገር በኢንተርፕራይዞችም ሆነ በሌሎች አካላት መስፋፋትና ወደ ተጠቃሚው ማድረስ ያስፈልጋል የሚሉት መምህሩ፤ ቴክኖሎጂው ችግር ፈቺና የህብረተሰቡን የመግዛት አቅም ያገናዘበ ስለሆነ ማንኛውም ሰው ወስዶ ሊጠቀምበት ይችላል ብለዋል::




**‹‹ፕሮሶፒስ ጁሊፍሎላ›› የተገኘውን የአረም አይነት ስተለያዩ አገልግሎት በማዋል ለማጥፋት የሚያስችል የፈጠራ ቴክኖሎጂ**

የአረሙ ተክል ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩ የታወቀው በ1980ዎቹ እንደሆነ የሚናገሩት አሰልጣኙ፤ በግብጽ፣ በዩጋንዳና በሌሎቹም አገራት ላይ መኖሩን ጠቅሰዋል:: ‹‹እኛ እንዳየነው አፍሪካ አገራት የከሰል ፕሪኬቱን ለማምረት የሚጠቀሙት በእጅ ነው፤ እኛ ግን ይዘን የቀረብነው ቴክኖሎጂ ቢስፋፋ በአፍሪካ አገራት ላይ ኤክስፖርት ማድረግ እንችላለን›› በማለት ቴክኖሎጂው ከአገር ውስጥ ባለፈ በውጭ አገር ተፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል::

ሌላኛው በክህሎት ውድድሩ ሥራቸውን ይዘው የቀረቡት አሰልጣኝ ከኦሮሚያ ክልል ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ሻሻመኔ ክላስተር የመጡት አሰልጣኝ መሐመድ ሙዴ ናቸው:: አሰልጣኝ መሐመድ፤ ገብስ መፈተጊያ ማሽን (barley grinding machine) በመባል ስያሜ የተሰጠውን የፈጠራ ቴክኖሎጂ ይዘው ነው የቀረቡት::

እሳቸው እንደሚሉት፤ እንደሚታወቀ በአገራችን በተለይ ገብስ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ያሉ እናቶች ወይም ሴቶች ገብስ ለመፈተግ የሚጠቀሙት ሙቀጫ ነው፤ አንድ ኪሎ ገብስ ለመፈተግ 20 ደቂቃዎች የሚወስድባቸው በመሆኑ ጊዜያቸው በከንቱ ሲባክን እንዲሁም ገብሱን ለመፈተግ የሚያወጡት ጉልበት ከፍተኛ በመሆኑ ለጉዳት ሲዳረጉ ኖረዋል::

አሁን ላይ በኮሌጁ የተሠራው የፈጠራ ቴክኖሎጂ የእናቶች ወይም የሴቶችን ድካም ከመቀነስ ባለፈ ጊዜን የሚቆጥብ ሲሆን፤ በ20 ደቂቃ ውስጥ አንድ ኩንታል ገብስ መፈተግ የሚያስችልም ነው::

ቴክኖሎጂው በተለይ ገብስ በብዛት በሚመረትበት አካባቢ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው የሚሉት አሰልጣኝ መሐመድ፤ ‹‹በእኛ አካባቢ ከገብስ ብዙ የምግብ አይነቶች እንደ ቆሎ፣ ቅንጬና የመሳሰሉትን ለማዘጋጀት በእጅጉ አስፈላጊ በመሆኑ አበርክቶው የጎላ ነው›› ይላሉ:: በገጠር አካባቢ ያሉ እናቶችና ሴቶችም ከገብስ ምግቦችም ለማዘጋጀት ገብስ ለመፈተግ የሚያወጡት ጉልበትና ድካም ይህንን ቴክኖሎጂ ለመሥራት ምክንያት መሆኑንም ገልጸዋል:: ‹‹እኛ የእናቶቻችንና የእህቶቻችንን ድካም መቀነስ የሚያስችል ፈጠራን በመስራት የመፍትሔው አካል መሆን እንችላለን በሚል ሀሳብ ለችግሮቻቸው መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችለንን ሥራ ነው የሰራነው ›› በማለት የቴክኖሎጂውን አስፈላጊነት አሰልጣኝ መሐመድ አስረድተዋል::

አሁን ላይ የፈጠራ ሥራው ለህብረተሰቡ ተላልፎ በሻሸመኔ አካባቢ ያሉ ወረዳዎች እየተጠቀሙበት ነው የሚሉት አሰልጣኝ መሐመድ፤ ሁሉም ጋ ባይደርስም አንዱ ከአንዱ እየሰማ ማሽኑን በመግዛት እየተጠቀመ እንደሆነም ጠቁመዋል::

በአካባቢው አንዳንዶች ገብስ ለመፈተግ ማሽን ይጠቀሙ እንደነበርም ጠቅሰው፣ ይህም በውጭ ምንዛሪ በውድ ዋጋ የሚገዛ እንደሆነ ነው የገለጹት:: በአማካኝ እስከ ሁለት መቶ ሺ ብር ድረስ ወጪን እንደሚጠይቅ ይናገራሉ::

አዲሱ የፈጠራ ቴክኖሎጂ ዋጋ ተተምኖለት በ35ሺ ብር ለህብረተሰቡ መቅረቡን ገልጸው፣ ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንጻር ዋጋው እጅግ ተመጣጣኝ እንደሆነ ይናገራሉ:: ይህ የፈጠራ ቴክኖሎጂ ከውጭ ከሚመጣው ቴክኖሎጂ የተቀዳ (ኮፒ) መሆኑንም ጠቅሰው፣ በአገር ውስጥ ግብዓች የተሠራ ነው ብለዋል::

አሁን ላይ ከተሜውም ቢሆን ገብስ በወፍጮ ቤት ለማስፈተግ የሚያወጣው ወጪ ቀላል የሚባል አይደለም የሚሉት አሰልጣኝ መሐመድ፤ በወፍጮ ቤት አንድ ኪሎ ገብስ ለመፈተግ ከሰባት ብር በላይ እንደሚጠየቅም ይገልጻሉ:: ማህበረሰቡ ማሽኑን በግልም ሆነ በጋራ እየገዛ እየተገለገለበት መሆኑን ተናግረዋል፤ ማሽኑ ረጅም ጊዜ የሚያገለግል መሆኑን ገልጸው፣ ህብረተሰቡ በሚፈልገው መጠንና ሁኔታ አሻሽሎ መስራት እንደሚቻልም ጠቁመዋል::

‹‹እኛ እንደ ኮሌጅ ይህንን ሥራ ካቀረብን ኢንተርፕራይዞች ደግሞ ህብረተሰቡ በሚፈልገው ልክ እያበዙ ለህብረተሰቡ መሸጥ ይችላሉ ›› የሚሉት አሰልጣኝ መሐመድ፤ ማሽኑ በማንዋል (በእጅ) ና በኤሌክትሪክ የሚሰራ መሆኑንም አስታውቀዋል፤ በሁሉም አካባቢ የሚገኝ ህብረተሰብ እንደፈለገው ሊጠቀምበት እንደሚችል ነው የገለጹት::

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ይህ ማሽን ህብረተሰቡ ዘንድ ደርሶ ተጠቅሞበት ድካም ሊቀንስ የቻለ በመሆኑ እንዲህ አይነት ቴክኖሎጂዎች መስፋፋት ይኖርባቸዋል:: ስለዚህ የኮሌጁ የፈጠራ ውጤት የሆነውን ቴክኖሎጂ በሁሉም አካባቢዎች እንዲስፋፋ ለማድረግ ከሚመለከተው አካል ሁሉ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል::

በመድረኩ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪያት ካሚል በበኩላቸው 3ኛው የክህሎት ውድድር አዳዲስ፣ ችግር ፈቺና እሴት ጨማሪ ቴክኖሎጂዎች ለእይታ የበቁበትና የክህሎት ውድድርን አንድ እርምጃ ወደፊት የሚያራምድ ከፍተኛ ፉክክር የተስተናገደበት መሆኑን አስታውቀዋል::

የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሥልጠና ተቋማት ብቻ እንዳልሆኑም ጠቅሰው፣ የማምረቻ ማዕከላት እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል:: ተቋማቱ ከኢንዱስትሪና ከፋይናንስ ተቋማት ጋር እንዲተሳሰሩ የሚያስችሉ የሪፎርም ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውንም ገልጸዋል:: በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የተመረቱ ተቀራራቢ ቴክኖሎጂዎች ተሰባስበው የሚጎለብቱበትና የተመረጡ ቴክኖሎጂዎች በስፋት የሚባዙበት የክረምት መርሃ ግብር በቅርቡ ይፋ እንደሚሆንም ጠቁመዋል::

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የንብረት ግብር ፋይዳ፤ ተስፋ እና ስጋት

ክብረአብ በላቸው

የንብረት ግብር አንድ ግለሰብ አሊያም ሕጋዊ አካል ለሚጠቀምበት ንብረት ለመንግሥት የሚከፍለው ገንዘብ ማለት ነው። በአብዛኛዎቹ የዓለም አገራት የንብረት ግብር የሚለካው ንብረቱ በየዓመቱ ተተምኖ የሚኖረውን ዋጋ መሠረት በማድረግ ነው።

የንብረት ግብር ኢትዮጵያ ውስጥ የተጀመረው በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን መንግሥት እንደሆነ መዛግብት ያሳያሉ። አብዮቱን ተከትሎ የመጣው ደርግ ባወጣው አዲስ ሕግ መሠረት የመሬት እና የጣሪያ ግብር ዜጎች እንዲከፍሉ ማድረግ ጀመረ። በዚህ ወቅት መሬት ግብር የሚጣልበት ንብረት ሳይሆን ዜጎች ከመንግሥት የሚከራዩት ነበር። ቢሆንም ዓመታዊ ግብር መክፈል ግድ ይል ነበረ። በ1983 ዓ.ም ወደ ሥልጣን የመጣው የኢሕአዴግ መንግሥት ጊዜ ያለፈበት ያለውን የንብረት ግብር እንደ አዲስ ከልሶት ተግባራዊ ቢያደርገውም ዘላቂ ሊሆን አልቻለም።

በርካታ የዓለማችን ከተሞች የንብረት ግብር ጥለው በሚሰበስቡት ገንዘብ ራሳቸውን ይደጉማሉ። አብዛኛውን ጊዜ የንብረት ግብር የሚጣልበት መሬት እና ሕንፃ ቢሆንም ተሽከርካሪዎች ላይም ግብር የሚጥሉ አገራት አሉ። የንብረት ግብር(ፕሮፐርቲ ታክስ) ከሌሎቹ የግብር ዓይነቶች የሚለየው በቀላሉ የሚደበቅ አለመሆኑ ነው። መንግሥት በሚሠራው የዋጋ ግምት መሠረት የአንድ ንብረት ዓመታዊ ዋጋ ተሰልቶ የሚጣል በመሆኑ ግለሰቦች ይህንን ግብር የሚደብቁበት መንገድ እንደማይኖራቸው የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልፃሉ።

የንብረት ታክስ በሌሎች አገሮች ከፍተኛ ወይም ትልቅ የገቢ ምንጭ እንደሆነ የሚነገር ሲሆን፣ ይህም በአጠቃላይ የንብረት ግብር ተብሎ የሚጠራ የግብር ዓይነት ነው። የንብረት ግብር በኢትዮጵያ ሁኔታ የጣራና ግድግዳ ግብር በሚል በደርግ ጊዜ በወጣ አዋጅ እስካሁን ድረስ የሚከፈልበት እንደሆነ ይነገራል፣ ሆኖም የክፍያ መጠኑ እጅግ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ብዙዎች ያነሳሉ። በደርግ ጊዜ የወጣው ሕግ መሻሻል እንደሚገባው ብዙኃን የሚስማሙበት ጉዳይ ሲሆን፣ ንብረት የራሱ የሆነ የግመታ ሥርዓት ሊኖረው እንደሚገባም ይነገራል። በተጨማሪም የታክስ ሥርዓቱ መሻሻል እንዳለበት እና ይህንንም መነሻ በማድረግ በረቂቅ ደረጃ ሕግ እንደተዘጋጀለት እየተገለጸ ይገኛል።

የምጣኔ ሀብትና ኢኮኖሚክስ ባለሙያው ዶክተር ዳዊት ሀዬሶ እንደሚናገሩት፤ ንብረት ላይ ሆነ ገቢ ላይ ታክስ የሚጣልበት የራሱ ዓላማ አለው። በአንፃራዊነት ሃብት ካለው ሰው ግብር በመሰብሰብ ዝቅተኛ ኑሮ ላለው ሆነ እንደ መንግሥት የልማት ሥራዎችን ለመሥራት እና ተገቢ የሃብት ክፍፍል በማድረግ ከድህነት ወለል በታች ያሉ ዜጎችን ሕይወት ለማሻሻል የሚተገበር የግብር ሥርዓት ነው ይላሉ።

በተለይ የንብረት ግብር ሲባል በእግሊዝኛ አጠራሩ Trickle down የሚባል የኢኮኖሚ ሥርዓትን የሚመለከት ሲሆን ማለትም አንድ ሀገር እያደገች ስትሄድ እና ሀብት እየተከማቸ ይሄዳል የሚለውን ጥቅል አባባል የሚመለከት ነው። ሀብት ካለው ወደ ሌለው ጠብ እያለ መሄድ አለበት፤ በዚህ ሂደት ድህነት ውስጥ ያሉ ዜጎች ከድህነት ለመውጣትና ኑሯቸውን ለመደጎም ያስችላቸዋል። ይህንን መነሻ በማድረግ ሀገር ግብር በሚከፍሉ ዜጎች እንድትደጎም ትደረጋለች። ለዚህም ገቢ በሚያገኙ ዜጎች ላይ የሥራ ግብር ፣የንግድ ትርፍ ግብር ፣በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ንብረት(ፕሮፐርቲ) ላይ ግብር ይጣላል።

ስለ ንብረት ግብር ስናወራ ትክክለኛነት ወይም ፍትሐዊነትን ከማስፈን አኳያ አንድ ሰው ካለው ላይ ነው ግብር የሚከፍለው ይላሉ ዶክተር ዳዊት፤ እንደ ምሳሌ ሲያነሱ ትልቅ ሕንፃ ኖሮት ብዙ ኪራይ ከሚሰበስብ ግብር ሳይቆረጥ በወር አራት ሺህ እና አምስት ሺህ ከሚያገኝ አንድ ግለሰብ ግብር እየሰበሰቡ በርካታ ሃብት እና ንብረት ካለው የንብረት ግብር አለመሰብሰብ በራሱ ፍትሐዊ አይደለም ብለዋል።

የሀገራችንን ሁኔታ ስንመለከት ሃብት ያለው ሰው ግብር ሳይከፍል የሚያልፍበት አጋጣሚ በርካታ መሆኑን



አቶ ዘካሪያስ ምናታ



ዶክተር ዳዊት ሀዬሶ

**ምሑራኑ እንደተናገሩት፤የንብረት ግብር ተግባራዊ ሲደረግ የመጨረሻ ጫናው ሄዶ በደሃው ዜጋ ላይ እንዳይወድቅ ይህንን የሚቆጣጠር አካል በተደራጀ ሁኔታ መፈጠር አለበት። ተቋማዊ እና ተጠያቂነት ያለበት የሕግ ከለላ ያለው፤ በባለሙያ የተደራጀ፤ የማስፈፀሚያ አቅም ያለው ተቋም ተመሥርቶ እጅግ ከፍ በለ ጥንቃቄ ሊከናወን ይገባል**

ምሑሩ ይናገራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ንብረት ማፍራት ከግብር ለመሸሽ ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሯል፤ አንድ ሰው በየጊዜው ትናንሽ ገቢዎች ላይ ኢንቨስት አድርጎ ትርፍ ከማግኘት ይልቅ (fixed asset) ቋሚ ነገር ላይ አውሎ ሃብት የማካበት ሁኔታ አለ ፤ይህ ደግሞ ግብር ወደ መሰወር የሚያስገባ ነው ብለዋል።

መንግሥት በማወቅ ሆነ ባለማወቅ ወይም ወቅቱ አልደረሰም በማለት ሳይሰበሰብ የቀረው በጣም ከፍተኛ የሆነ ግብር አለ፤ ስለዚህ ይህንን የንብረት ግብር በተገቢው ሁኔታ መሰብሰብ ከተቻለ በአሁኑ ጊዜ በእጅጉ እየጨመረ የመጣውን የሕዝብ ፍላጎት ለማሟላት፤ ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና ፍትሐዊ የሃብት ክፍፍል ከማስፈን አኳያ ሰፊ ድርሻ የሚጫወት ይሆናል ብለዋል።

በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ መምህር እና የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዘካሪያስ ምኖታ በበኩላቸው፤ የንብረት ግብርን በተገቢው ሁኔታ መሰብሰብ የሀገር ውስጥ ገቢን በማሳደግ ለዜጎች መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት አይነተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ይላሉ።

በመሠረቱ ታክስ የሚሰበሰበው መልሶ ለሕዝብ ጥቅም ለማዋል እንደሆነና በመሠረተ ልማት ላይ ማለትም በመንገድ፣ በውሃ፣ በመብራት እና መሰል ዘርፎች ላይ ከዋለ ደግሞ የዜጎችን ሕይወት የመለወጥ አቅሙ ከፍተኛ እንደሆነ ይናገራሉ። ይህ ደግሞ እንደ ሀገር ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ለሀገር እድገት አስተዋፅዖ የጎላ ይሆናል። ኢንቨስትመንት መሳብ ከተቻለ ደግሞ የሥራ ዕድል ይፈጠራል ፤ይህ ደግሞ ለኢኮኖሚው ዕድገት አጋዥ ነው ብለዋል።

ነገር ግን የንብረት ግብር አሠራሩን ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ የሕግ ማሻሻያ ይፈልጋል የሚሉት አቶ ዘካርያስ የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ ከመንግሥት እና ከሕዝብ ከሚለው ወጥቶ የግል መሆንን እንደሚጠይቅ ይጠቁማሉ። በመጀመሪያ በተገቢው ሁኔታ ለማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እናውለው ካልን ከሕግ አንፃር ብዙ የግድ መሻሻል ያለባቸው የመሬት እና የንብረት ነክ ጉዳዮች አሉ ይላሉ።

ዶክተር ዳዊት ሀዬሶ በበኩላቸው ሲናገሩ፤ አፈፃፀሙ ላይ ችግር እንዳይፈጠር በተለይ የዋጋ ግመታ ላይ አሠራሩ የግለሰቦች ጣልቃ ገብነት እንዳይኖር ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ይላሉ። መስፈርቶችን ማዘጋጀት እና የሚተገበርበትን መንገድ ግልጽ እና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ለመሥራት ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል ብለዋል። ካልሆነ አንድ ሰው በትንሽ ንብረት ትልቅ ግብር በሌላ መልኩ ደግሞ ትልቅ ንብረት ይዞ ጥቂት የንብረት ግብር የመክፈል ሁኔታዎች ሊያጋጥም እንደሚችል ያላቸውን ስጋት ያስቀምጣሉ።

በሌላ በኩል የታክስ ጫናው ዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል ላይ እንዳያርፍ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግና የንብረት ግብር ዋነኛ ዓላማ አቅም ካለው ግብር ከፋይ በመውሰድ ዝቅተኛውን የኅብረተሰብ ክፍል መደጎም መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል ይላሉ።

ነገር ግን በዚህ ሂደት አብዛኛው ዜጋ የራሱ ቤት የሌለው እና በኪራይ ቤት የሚኖር እንደመሆኑ ይህንን ምክንያት አድርጎ ሌላ ማኅበራዊ ቀውስ እንዳይፈጠር ሂደቱ በጥንቃቄ መመራት አለበት የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

ቀድሞ መከላከሉ እንዳለ ሆኖ ይህንኑ ሰበብ በማድረግ በተከራዮች ላይ ዋጋ ጨምሮ በተገኘ ሰው ላይ ሲገኝ ተጨማሪ ግብር በመጨመር መቀጣጫ በማድረግ ምክንያታዊ ያልሆነ ጭማሪ እንዳይኖር መደረግ እንዳለበት ያስረዳሉ። እንደ ምሳሌ ሲያነሱ፤ አንድ ሺህ ብር የሚያከራይ ሰው በዚህ ምክንያት አምስት መቶ ብር ከጨመረ ያንኑ ብር ለመንግሥት እንዲከፍል ከተደረገ አከራይ የመጨመር ፍላጎት አይኖረውም። ከዚህ በተጨማሪ ጠንከር ያለ ቅጣት ከተጣለም የኪራይ ዋጋ ለመጨመር አይነሳሳም። ይህንን አሠራር የሚያስጠብቅ አካል ግልፅነት የሰፈነበት መሆን አለበት ። አንዳንድ ሀገራት ላይ እንደተስተዋለው ለሙስና እና ማጭበርበር በር ከፋች እንዳይሆን መንግሥት አሠራሩን በጥንቃቄ እና ግልፅ በሆነ መንገድ መምራት አለበት ብለዋል ዶክተር ዳዊት።

ታክስ ሲጣል ሁለት መርሆዎች ታሳቢ መደረግ አለባቸው የሚሉት አቶ ዘካሪያስ፤ የመክፈል አቅም እና የተጠቃሚነት መርሐ በዋናነት መሠረት ተደርጎ እንደሚተገበር ዶክተር ዳዊት ያስረዳሉ። ስለዚህ እነዚህ ሁለት ነገሮች ቀጣይነት ባለው መልኩ ታሳቢ ተደርገው መያዝ እንዳለባቸው ያብራራሉ።

የመሬቱ ወይም የንብረት የአካባቢ የገበያ ዋጋ በትክክል መጠናት እንደሚኖርበትና ከብዙ ዓመታት በኋላ ይህ ቦታ ምን ያህል ዋጋ ያወጣል የሚለውን በማስላት የዛሬው ተመን ሊወጣ እንደሚገባም ይጠቁማሉ። ይህ እንዲሆን ደግሞ በመላው ሀገሪቱ ዳታ ቤዝ ተዘጋጅቶለት ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል ብለዋል። አሠራሩም በመላው ሀገሪቱ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ መመራት እንዳለበትና አካታች የሆነ ፍትሐዊ የሆነ የማኅበረሰቡን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ያገናዘበ መሆን ይገባዋል ይላሉ። በተጨማሪ የንብረት ግብር የማይክሮ ኢኮኖሚያዊ መረጋጋት በማይጎዳ መልኩ እና ለዋጋ ግሽበት ተጨማሪ መንስኤ በማይሆን መልኩ ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ይጠቁማሉ።

እንደ ዶክተር ዳዊት ገለጻ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ በባለሙያ የተደገፈ አሠራር ሊኖር ይገባል። ተጠያቂነት ያለው ተቋም የሚመራው ሆኖ ያለውን የመሬት ሁኔታ የመኖሪያ ፣የንግድ ፣የኢንዱስትሪ አካባቢያዊ መስተጋብር በአግባቡ በመለየት መሥራት አለበት። የንብረት ግብር የምጣኔ አግባቡ ደግሞ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ በመውሰድ ተራውን ዜጋ ሆነ ባለሀብቱን በማይጎዳ መልኩ ሊሠራ ይገባል ።

አቶ ዘካርያስ በበኩላቸው አንዳንድ ሀገራት የንብረት ግብር ያስከፍላሉ ነገር ግን ከአጠቃላይ ግብር ተቀናሽ ያደርጋሉ። አሁን ከኢትዮጵያ አንፃር ይህ አሠራር ሰለሌለ ተደራራቢ ታክስ እንዳይፈጥር እና ለዜጎች ወይም በኢንቨስትመንት ለተሠማሩ ሰዎች ወይም ለባለሀብቶች የምሬት ምንጭ እንዳይሆን እና ለኢንቨስትመንት ፍሰቱ ማነቆ ሆኖ እንዳይመጣ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ይላሉ።

ንብረቱ ያለበት ቦታ ሌላው ወሳኝ ነገር ነው የሚሉት አቶ ዘካሪያስ ልየታ ሲደረግ የተለያየ ደረጃ ያላቸውን ቦታዎች እኩል መታየት እንደሌለባቸው ይጠቁማሉ። አሁን እየተተገበረበት ያለው ሁኔታ በጥናት እና በተደራጀ መልኩ ወደ ትግበራ የገባ ስላልሆነ በተለይ በዋጋ ትመና ወቅት በጥቅም በመመሳጠር ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ እንዳይሆን ያላቸውን ስጋት ገልፀው ጉዳዩ ቀለል ተደርጎ ሊታይ የማይገባው ትልቅ ትኩረት የሚሻ እንደሆነ አመልክተዋል።

በአጠቃላይ አቶ ዘካሪያስ እንደተናገሩት፤እውነተኛ የንብረት ግብር ዳታ ቤዝ ወይም የመረጃ ሲስተም መተግበር አለበት። ይህም ዲጂታላይዝ ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም ማን? የት? ምን ያክል መሬት ወይም ንብረት አለው የሚለውን ሰንዶ ስለሚያስቀምጥ ግልፅነት ለማስፈን ያግዛል ብለዋል።

ምሑራኑ እንደተናገሩት፤የንብረት ግብር ተግባራዊ ሲደረግ የመጨረሻ ጫናው ሄዶ በደሃው ዜጋ ላይ እንዳይወድቅ ይህንን የሚቆጣጠር አካል በተደራጀ ሁኔታ መፈጠር አለበት። ተቋማዊ እና ተጠያቂነት ያለበት የሕግ ከለላ ያለው፤ በባለሙያ የተደራጀ፤ የማስፈፀሚያ አቅም ያለው ተቋም ተመሥርቶ እጅግ ከፍ በለ ጥንቃቄ ሊከናወን ይገባል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ሴቶችን ወደከፍታ ያወጣል የተባለለት ኤክስፖ

ጽጌረዳ ጫንያለው

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ግማሹን የሚሸፍነው የሴቶች ቁጥር እንደሆነ በተደጋጋሚ ይገለጻል:: ሆኖም የኅብረተሰቡን ግማሽ ያህል ያዙ ይባል እንጂ ተጠቃሚነታቸው እዚህ ግባ የሚባል ነው ለማለት አይቻልም:: በተለይም ከኢኮኖሚያዊ ተሳትፏቸውና ተጠቃሚነታቸው ጋር ተያይዞ የሚነሱ ነገሮች አሁንም መፍትሄን የሚፈልጉ እንደሆኑ ግልጽ ነው:: ምክንያቱም ዛሬም መብቶቻቸው ሳይቀር ከወንዶች ጋር ሲነጻጸሩ እጅግ ያነሰ እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ::

ለአብነት በኢትዮጵያ አሁንም ድረስ ያልተፈታ የመሬት ባለቤትነት መብት አለ:: ፍትሐዊ የሥራ ክፍፍል ጉዳይም በወንዶችና ሴቶች መካከል ልዩነቱ የጎላ ነው:: ይህ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን በብዙ መልኩ ይገድበዋል:: በአግባቡ እንዳይጠቀሙና ራሳቸውን እንዳያወጡ ያደርጋቸዋል:: በተለይም ይህ ነገር በስፋት የሚስተዋለው በኢትዮጵያ ገጠራማ ክፍሎች እንደሆነ እሙን ነው:: አሁን ድረስ አባት ለሴት ልጁ ሀብት የማውረስ ወይም እንድታስተዳድር እድል መስጠት ባህል አልሆነም::

በአንዳንድ ሥራዎችም ኃላፊነት ለመስጠት እጅጉን ይፈራል:: ምክንያቱም ብቃቷን እንኳን ቢረዱ ትወልድና ስራችንን ታስተጓጉለዋለች ትባላለች:: ይህ ደግሞ በተለይም ከሥራ ቅጥር ጋር በእጅጉ ይቆራኛል:: ከገጠሩ ይልቅ ከተማው ላይ ይሰፋልም:: ከተማው ላይም ቢሆን ከመንግስት ተቋማት ይልቅ ግሉላይ በስፋት የሚያጋጥም ነው:: ስለዚህም ነፍሰጡር የሆነች እናት እንዳትቀጠር ጭምር ትሆናለች:: እናም ይህን መሰል ችግሮች ሴትን ልጅ የፈለገችው ቦታ ላይ እንድትደርስ አላደረጋትም:: ታዲያ መፍትሄው ምንድነው? ከተባለ ሰሞኑን የተሰማው ነገር እጅግ ተስፋ የሚሰጥ ይመስላል:: የነጋዴ ሴቶች ኤክስፖ፤ የሀሳቡ ጠንሳሽ ማሌሳ ኤቨንትና ፕሮዳክሽን ነው:: ሀሳቡን የሚያስፈጽመው ደግሞ ከዚህ ተቋም ጋር በመተባበር የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲሆን፤ ሚኒስቴር መስሪያቤቱ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ችግሮችን መፍታት የሚቻለው በራስ አቅም ብቻ ሳይሆን ከአጋር አካላት ጋር በመስራት ነው ብሎ ያምናል። በአይነቱ ልዩ የሆነና ብዙ ሴቶችን ወደ ሥራ ያስገባል የተባለለትን ኤክስፖ እውን እንዲሆንም ሰርቷል::

ይህ ኤክስፖ «Connect, Create, Accelerate» በሚል መሪ ሀሳብ የሚካሄድ ሲሆን፤ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ የበላይነቱን ወስዶ ሌሎችን የመንግስት ተቋማት በማካተት እየተንቀሳቀሰ የሚገኝበት ነው:: በርከት ያሉ አጋር አካላትም ገብተውበታል:: ለአብነት ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጠቃሾች ናቸው::

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በዚህ ኤክስፖ ሲሳተፍ አገልግሎት ሰጪ ሴቶች ይታሰባሉ:: ስለዚህም አምራቹን ዘርፍ ያሳትፋል:: ስራና ክህሎት ሚኒስቴር ሲታሰብ ደግሞ ሥራና ሰራተኛን ከማገናኘት አንጻር ያሉ ተግባራትን ያከናውናል:: ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂን ስናነሳ ደግሞ ፈጠራንና ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂን በንግዱ ዘርፍ ሴቶች እንዲመለከቱ የሚያስችል ነው:: ስለዚህም በአጠቃላይ እነዚህ ተቋማት በንግዱ ሥራ ላይ ሴቶች እንዴት መጠቀም ይችላሉ በሚል የሚያግዙ ይሆናል::

ለመሆኑ ኤክስፖው ምን ለየት ያደርገዋል፤ ምንስ ጥቅም አለው? ከተባለ ለጋዜጠኞች በተሰጠው መግለጫ እንደተገለጸው፤ የነጋዴ ሴቶች ኤክስፖው ምርታቸውን ከመሸጥ እና ከማስተዋወቅ ባለፈ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሻሻል እንደ ማስፈንጠሪያ መድረክ ሆኖ ያገለግላል:: ማለትም መድረኩ ሴቶችን ያገናኛል፤ አዳዲስ ነገሮችን ፈጣሪ ያደርጋል:: በተጨማሪም የሚሰሩትን የሚያበረታታና ወደተሻለ መስመር የማስገባት እድል የሚፈጥር ነው::

የነጋዴ ሴቶች ኤክስፖው ከሰኔ 7 እስከ ሰኔ 9 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ በስካይላይት ሆቴል የሚከናወን ሲሆን፤ ሴቶች በስራ ፈጠራ፣ በአምራችነት፣ በንግድ፣ በገበያ ትስስር፣ በኢንዱስትሪ መሰረተ ልማት እና ተወዳዳሪነት ዙሪያ ያላቸውን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት የሚያሰፉበት ነው ተብሎለታል::

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ አለሚቱ ኡሙድ ኤክስፖውን በተመለከተ በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ይህ ኤክስፖ የሚያሳየን አንድ ነገር

> **ከምርት ሽያጩ እና ከሥልጠናው ጎን ለጎን በሥራ ፈጣሪነት፣ ጊዜውን በዋጀው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ስለሚሳተፉ ሴቶች እንዲሁም በሌሎችም ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይትም ይካሄዳል:: ይህ ደግሞ በየዘርፉ ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል:: ለአብነት ስኬታማ የሆኑ ሴቶች ልምዳቸውን ያጋሩበታል**

አለ:: ይህም በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ ሴቶች ያላቸው ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል:: ሆኖም አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ሴት ስራ ፈጣሪዎች፣ አምራቾች፣ የንግድ ተቋም ባለቤቶች እና መሪዎች ከብድር አቅርቦት፣ ከወለድ ምጣኔና ከእፎይታ ጊዜ፣ ዘላቂ የገበያ ትስስር ከመፍጠር፣ ከምርት ማቀነባበሪያና ማሳያ፣ ከመስሪያ ቦታ፣ ከቴክኖሎጂ ተደራሽነትና ስልጠናዎችን ጋር የተያያዙ ችግሮች ይገጥሟቸዋል:: ይህ ደግሞ ባሰቡት ልክ እና ፍጥነት ችግሮቻቸውን ተቋቁመው እንዳያድጉና በድካማቸው ልክ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማነቆ ሆኖባቸዋል:: በመሆኑም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እየታየ ያለውን አበረታች ውጤትና የለውጥ ጅማሮ በሁሉም ዘርፎች ፍትሃዊነትና ዘላቂነት ባለው መልኩ አጠናክሮ ለማስቀጠል እና የሴቶችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በትኩረት እንዲሰራ ሆኗል::

ሴቶች ያሉባቸው ችግሮች በርካታ እንደሆነ የጠቆሙት ወይዘሮ አለሚቱ፤ ከችግሩ ስፋት አኳያ በመንግስት ብቻ በሚደረግ ጥረት የሚስተዋሉ ችግሮችን መቅረፍ አዳጋች ነው:: ስለሆነም የልማት አጋራት፣ የግል ባለሃብቶች እና ሌሎች የዘርፉ ተዋናዮች በትብብር ሊሰሩ ይገባል:: ይህ ኤክስፖም የሚያሳየው ይህንን መተባበር ነውና ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚገባ አሳስበዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያግዙ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል:: የሴቶችን ኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከሚሠሩ ሥራዎች መካከል ደግሞ አንዱ ለነጋዴ ሴቶች ገበያ ማፈላለግን ላይ ያተኮረ ነው:: እናም ይህ ኤክስፖ ስኬታማ እንዲሆን ከባለድርሻ አካላት ጋር እንዲሰራ ሆኗል::

በነጋዴ ሴቶች ኤክስፖ ከ100 በላይ ድርጅቶች የሚሳተፉ ሲሆን፤ በተለያዩ የንግድ ዘርፎች የተሰማሩ ሴት ሥራ ፈጣሪዎች፣ አምራቾች እና የንግድ ተቋም መሪዎች ምርትና አገልግሎታቸውን ይዘው እንደሚቀርቡ ይደረጋል:: አብዛኞቹ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ናቸው:: ምክንያቱም እንደአገር ያለንበት በኢኮኖሚ ያለው ተጠቃሚነት እጅግ አናሳ ነው:: ስለዚህም ያንን ለመፍታት እንደነዚህ አይነት አማራጮች ሁነኛ መፍትሄ ናቸውም ሲሉ አብራርተዋል::

ወይዘሮ አለሚቱ ኤክስፖው ሴት አምራቾችን፣ ነጋዴዎችን፤ ሥራ ፈጣሪዎችን እና የመሪነት ሚናቸውን በመወጣት ላይ የሚገኙ ሴቶችን የሚያበረታታ፤ ሴቶች ፍትሐዊ እና በፆታ እኩልነት ላይ የተመሠረተ እገዛ እንዲያገኙ ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም የገበያ ተወዳዳሪነትና ዘላቂ የገበያ ትስስር ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲሁም በሥራ ፈጠራ ላይ መሳተፍ ለሚፈልጉ ታዳጊ ሴቶች የሚኖረው ሁለንተናዊ ፋይዳና አበርክቶ ከፍተኛ ነው ሲሉ በመግለጫቸው አስረድተዋል::

በኤክስፖው የሚሳተፉት ሴቶች ከ35 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ጎብኚዎች ምርታቸውን የሚሸጡና የሚያስተዋውቁ መሆኑን የገለጹት ደግሞ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሴቶችን ማብቃት መሪ ስራአስፈጻሚ ወይዘሮ ወይንሸት ገሪሶ ሲሆኑ፤ የንግድ ስራ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቀደምት እና የኢኮኖሚ ማዕከል ሆኖ የቆየ ቢሆንም እስከ አሁን የአገሪቱን የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ንግድ ስርዓትን በአግባቡ የሚመራ፣ አጠቃላይና ወጥ የሆነ የንግድ ፖሊሲ እንዳልነበረ ያነሳሉ::

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ፖሊሲው አለመኖሩ በፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አፈፃጸም እና በንግድ ዘርፉ ላይ ያሉ የንግድ እድሎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ስታንዳርዶች በተመለከተ የአሰራር ወጥነት ችግሮች ይስተዋላሉ:: በተለይም ሴቶችን በተመለከተ ብዙ ክፍተት ይታይበት ነበር:: እናም በዘንድሮው ዓመት ይህንን ከማስተካከል አኳያ ትልልቅ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ:: አንዱ ፖሊሲውን የማሻሻል ሥራ ሲሆን፤ ከዚህ ጋር ተያይዞም በቀጣይ የሚከናወኑ በርካታ ተግባራት እንደሚኖሩ አንስተዋል::

የንግድ ፖሊሲው መነሻ አገራችን ቅድሚያ ትኩረት በምትሰጥባቸው እና የዓለም አቀፍ ንግድ ትኩረት የሆኑትን ምርትና አገልግሎቶች እንዲሁም የአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፎች እና በአሁኑ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ወሳኝ በሆነው የንግድ ሰንሰለቶች ላይ ይሆናል:: ይህ ደግሞ ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም በእኩል ደረጃ የሚሳተፉበት መሆን ይገባዋል:: እናም ከንግድ አንጻርና ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ጋር ተያይዞ ሴቶች እንዲልቁ ማድረግ ላይ መስራት ያስፈልጋል:: ለዚህ ደግሞ የሴቶችን አቅም የሚገነቡ ተግባራት ላይ መሥራት ግድ ነውና እነዚህን ሥራዎች ለማከናወን ኤክስፖው ከፖሊሲው ቀጥሎ የሚተገበር አዋጪ ሥራ መሆኑንም ጠቁመዋል::

በኤክስፖው ምርት እና አገልግሎታቸውን ከመሸጥና ከማስተዋወቅ ባለፈ በተለያዩ የንግድ ዘርፎች የተሠማሩ ሴት ሥራ ፈጣሪዎች፣ አምራቾችና የንግድ ተቋም መሪዎች እንዲሁም በየትኛውም የሥራ ደረጃ ላይ ያሉ ሴቶች ስለ ፋይናንስ ቴክኖሎጂ፣ ስለዲጂታል ማርኬቲንግ፣ ስለ ገበያ ጥናት በመሳሰሉት መሠረታዊ ጉዳዮች እንዲረዱ የሚሆኑበትም ነው ያሉት ደግሞ የነጋዴ ሴቶች ኤክስፖ ክሬቲፍ ዳይሬክተር ሲሃም ፈይሰል ናቸው :: ምክንያቱም ይህ ኤክስፖ በሦስት ተከታታይ ቀናት ቆይታው በሺዎች ለሚቆጠሩ ተሳታፊዎች ልዩ ልዩ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎች ይሰጥበታል።

ከምርት ሽያጩ እና ከሥልጠናው ጎን ለጎን በሥራ ፈጣሪነት፣ ጊዜውን በዋጀው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ስለሚሳተፉ ሴቶች እንዲሁም በሌሎችም ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይትም ይካሄዳል:: ይህ ደግሞ በየዘርፉ ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል:: ለአብነት ስኬታማ የሆኑ ሴቶች ልምዳቸውን ያጋሩበታል:: በዚህም በርካታ ሴቶች ልምድ እንዲቀስሙ ይሆናሉ:: በተመሳሳይ ባለድርሻ አካላት ስለሚሰጧቸው አገልግሎቶች በሰፊው ያብራራሉ:: ይህም በሥራ ውስጥ ያለ አገልጋይነት ምን ይመስላል የሚለውን ሀሳብ ሴቶች እንዲቀስሙ ይሆኑበታል::

የኤክስፖው ዋና አስተባባሪና የማሌሳ ኢቨንት ስራ አስኪያጅ ሰላማዊት ደጀን በበኩላቸው፤ በኤክስፖው ታዳጊ ሴት ሥራ ፈጣሪዎች የበለጠ ይበረታታሉ፤ ድርጅቶች ተቋማቸውን እንዴት ማሳደግ እንዳለባቸው ይማራሉ:: ገና ወደ ንግድ ለመግባት ያሰቡ ብቻ ሳይሆኑ በየትኛውም የሥራ ደረጃ ላይ ያሉ ሴቶች ጊዜውን የዋጀ ሥልጠና ያገኛሉና ቀጣይ ጉዟቸውን ያስተካክላሉ ይላሉ::

ኤክስፖው በተለይም ከ18 ዓመት እስከ 65 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሴቶች የሚጠቀሙበት እንደሆነ የሚገልጹት አስተባባሪዋ፤ ለሥራ ቅጥር የሚመጡትን ለማስተናገድ የሚችሉ 14 ፈቃደኛ የሆኑ ሥራ ፈጣሪ ተቋማት መዘጋጀታቸውንም በመግለጫው ወቅት አንስተዋል:: ኤክስፖው በተመሳሳይ ሥራ እንዴት መጀመር እችላለሁ፤ ማን ጋር የምፈልገውን አገኛለሁና ምን አይነት ሥራ ለእኔ ተመራጭ ነው የሚለውን ለመረዳት የሚችሉበት ነው:: ምክንያቱም በየዘርፉ ስልጠና የሚሰጡ አካላት አሉ:: በተለይም ሴቶች ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው የሥራ መስኮች ላይ አቅማቸውን እንዲገነቡ የሚሆኑበት ነው:: እናም ተሳታፊዎች ወደኤክስፖው ሲመጡ የተለየ አቅም ለማግኘት፣ የስራ አጋር ለመተዋወቅ፣ ሥራቸውን የተሻለ ለማድረግና ሥራ ለማግኘት በመሆኑ እድሉ ባያልፋቸው መልካም እንደሆነ ያስረዳሉ:: እኛም ኑና የተሰጣችሁን እድል ተጠቀሙ በማለት ለዛሬ የያዝነውን አበቃን:: ሰላም!!

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

በተለያዩ ዘመናት ከወጡ ከቀድሞ የአዲስ ዘመን ገጾች እየቀነጨብን ለአዲሱ ትውልድ የድሮውን የምናሳይበት፣ ለአንጋፋው ትውልድ ደግሞ የምናስታውስበት አዲስ ዘመን ድሮ ዓምድ ዛሬም የተለያዩ ጉዳዮችን ይዞ ቀርቧል:: ወደ ኋላ በረዥሙ ተጉዞም ከ1950ዎቹና በማስታወስ ማረፊያውን በ2000 ላይ አድርጓል። የንጉሱ ባለቤት እቴጌ መነን ያደረጉት አንድ የሻምፓይን ግብዣ ነበር። ትልቁ የውቅሮ ድልድይ ተሰርቶ ለአገልግሎት ክፍት መደረጉ፣ በአሁኑ ወቅት የሚታየው የቦረና ድርቅ ከዚህ ቀደምም በአንድ ወቅት ተከስቶ የነበረ ስለመሆኑም ይነግረናል። በሕዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ላይ የተጠመደ ፈንጅ ፈንድቶ የንጹሃኑን ሕይወት የቀጠፈበት አሳዛኝ ክስተት፣ ጋንሱ የተሰኘው ታዋቂው የቻይና የሙዚቃ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በሚሊኒየሙ ሰሞን ድምቀት ሆኖ አልፏል። የአበበ ቢቂላ በባይሎጂስቶች መመርመር እንዳለበት የወጣ ዘገባም አለ። በተጨማሪ ደግሞ 'ሰው ምን ይላል?' ከሚለው ገጽ ላይ ለቅምሻ ያህል ተካቶ ቀርቧል::

### የተደረገ የሻምፓይን ግብዣ

ስለ ልዕልትነታቸው በደህና መገላገል በእዚሁ ቀን ከጠዋቱ በአንድ ሰዓት ተኩል ላይ 21 ጊዜ መድፍ ተተኩሷል። ግርማዊት እተጌ መነን ስለ ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ በደህና ሴት ልጅ መገላገል፣ ግንቦት አራት ቀን ትናንት ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ በገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ለልዑላት ንጉሣውያን ቤተሰብና ደስታቸውን ለመግለጥ ለሄዱት ክቡራን ሚኒስትሮችና መኳንንት፣ ክቡራት፣ ወይዛዝርት የሻምፓይን ግብዣ አድርገዋል:: **(አዲስ ዘመን መጋቢት 14 ቀን 1951 ዓ.ም)**

### የውቅሮ ድልድይ ተሠርቶ ስተሽከርካሪ ተከፈተ

ከአዲስ አበባ ወደ አስመራ መንገድ በ816 ኪሎ ሜትር በውቅሮ ከተማ የሚገኘው ትልቅ ድልድይ ባለፈው ጥቅምት 29 ቀን 1958 ዓ/ም ውሃ ሰርስሮ የድልድዩን መሠረት ለሁለት ስለከፈለው በጠቅላይ ግዛት የአውራ ጎዳና ሠራተኞች ችሎታ በደንብ ስለተሠራ የፈረሰው ድልድይ ከሠባት ወር በኋላ ተሽከርካሪዎች ሊተላለፉበት ችለዋል። (አዲስ ዘመን ታህሳስ 9 ቀን 1958 ዓ.ም)

በቦረና ዞን በእንስሳት ላይ የተከሰተውን የውሃና መኖ እጥረት ለማስወገድ ጥረት እየተደረገ ነው

አዲስ አበባ (ዋኢማ)፤-በእንስሳት ላይ የተከሰተውን የውሃና መኖ እጥረት ለማስወገድ የውሃና ሳር አቅርቦት እያከናወነ መሆኑን የኦሮሚያ አደጋ መከላከል ዝግጅትና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን አስታወቀ::

.............

ረዘም ያለ መንገድ መሄድ የሚችሉትን የቤት እንስሳት ከአከባቢው ማንቀሳቀስ መቻሉን ጠቁመው፣ ለጥጆችና ላሞች ባሉበት የውሃና ሳር አቅርቦት እየተደረገ ነው:: **(አዲስ ዘመን ታህሳስ 7 ቀን 2000 ዓ.ም)**

### በሕዝብ ማመሳለሻ አውቶብሶች ሳይ የተጠመደ ፈንጅ ፈንድቶ በሰላማዊ ዜጎች ሳይ ጉዳት ደረሰ

አዲስ አበባ-(ኢዜአ)፡-ከሁመራ መናኸሪያ ወደ ሽሬ ከተማ በመጓዝ ላይ በነበረ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ላይ በሻዕቢያና ተላላኪዎቹ የተጠመደ ፈንጅ ከትላንት በስቲያ ከጠዋቱ 1 ሰዓት ከ15 ደቂቃ ላይ ፈንድቶ በሰላማዊ ዜጎች ላይ ጉዳት መድረሱን የሁመራ ዞን ፖሊስ ጽህፈት ቤት አስታወቀ::

ጽህፈት ቤቱ እንደገለጸው፣ በፈንጂው ጥቃት 8 ሰዎች ወዲያውኑ ሲሞቱ በ27 ሰዎች ላይ ደግሞ ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ ደርሷል።

የኤርትራ ወጣቶችና ወታደሮች በብዛት እየከዱ ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸው ያሳሰበው ሻዕቢያ በተደጋጋሚ ጊዜ በእራሱና በተላላኪዎቹ አማካኝነት በሁመራ አካባቢ ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ሥፍራዎች የሽብር ጥቃት ሲሞክር መቆየቱን ጽህፈት ቤቱ ገልጿል። (አዲስ ዘመን ጥቅምት 24 ቀን 2000 ዓ.ም)

ታዋቂው የቻይና ጋንሱ ሙዚቃ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጣ ተገለጸ

አዲስ አበባ፡- ታዋቂው የቻይና ጋንሱ የሙዚቃ ቡድን አዲሱን ሚሊኒየም ምክንያት በማድረግ ከመጋቢት 11 እስከ መጋቢት 14 በአዲስ አበባና በመቀሌ የተለያዩ ዝግጅቶችን ያቀርባል::

የሙዚቃ ቡድኑ በኢትዮጵያ ተገኝቶ ትርዒቱን ማቅረቡ ሚሊኒየሙ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ መላው ዓለም የሚያከብረው መሆኑን የሚያመለክት እንደሆነ ጠቁመዋል:: **(አዲስ ዘመን የካቲት 29 ቀን 2000 ዓ.ም)**

### የአበበ ቢቂላ ሰውነት በባይሎጂስቶች ይመረመራል

የሰውን ሕዋሳት የሚመረምሩ ሳይንቲስቶች የሁለት ጊዜ የማራቶን ባለድል የሆነው የአበበ ቢቂላን ሰውነት ለመመርመር አስበዋል:: ዶክተር ኢቢዎርዚግተን የዓለም የባይሎጂ ምርምር ዳይሬክተር የሆኑት የመቶ አለቃ አበበ ቢቂላ ሰውነት ለምርምር ቢቀርብ ማራቶን በቀላሉ እንዴት ለማሸነፍ እንደሚቻል ይታወቅ ነበር ብለዋል::

አበበ ቢቂላ ሁለት ጊዜ የማራቶን ባለድል የሆነበት ምክንያት፣ የሚኖርበት አካባቢ ደጋማ ስፍራ ስለሆነ ሰውነቱ ኦክስጂን የተባለውን አየር እንደልቡ ስላገኘ ነው ሲሉ ዶክተሩ አስረድተዋል::

ጤናማ አየርና ጤና ሰውነት ሲገናኙ ኃይልን ለማስገኘት እንደሚችሉ ተናግሮአል:: **(አዲስ ዘመን ህዳር 20 ቀን 1958 ዓ.ም)**

### ሰው ምን ይሳል?

ሴቶች ከሁሉም አብልጠው የሚጠብቁት ሚስጥር ምንድነው?

**....ዕድሜያቸው.....**

አንድ ሺህ ሰዎች ራቁታቸውን ከፊትህ ቆመዋል። 500 ሴቶችና 500 ወንዶች ሆነው አዳምና ሔዋን ከመካከላቸው ቢኖሩ ሁለቱን እንዴት ትለያቸዋለህ?

........አዳምና ሔዋን ከሴት ማኅፀን ስላልወጡ እምብርት የላቸውም.....

ዘማች መምህር

### ስወይዛዝርት ገጽ አዘጋጅ

አዲስ አበባ ነፍሳቸውን ይማርና አለቃ ገብርሃና የታወቁ ቀልደኛ ነበሩ ይባላል። እውነት ነው እንዴ? ከጨዋታቸው አንዱን ቢገልጡልኝ 'የምታውቁት ነገር እንዳለ ' እያሉ ከሚጽፉት ታሪክ ውስጥ ይህም ለእኔ አንዱ ስለሆነ ደስ ይለኛ ነበር።

ወንድሙ እርገጤ (ከአርባ ምንጭ)

-ስለ አለቃ እኛም ሲሉ ሰማን እንጂ በርግጥ ቀልደኛ ናቸው ብለን አናረጋግጥሎትም። የጥንቱን የሌሎችን ቀልድ በአለቃ ላይ አድርገውታል። የአለቃን ቀልድ እስትናገኝ ቀጠሮ ብንጠይቆት እናስከፋዎት ይሆን?

# ዓለም አቀፍ

## በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው የነበሩት የቀድሞዋ የስኮትላንድ መሪ ተለቀቁ



የቀድሞ የስኮትላንድ ተቀዳሚ ሚኒስትር ኒኮላ ስተርጅን ያለተጨማሪ የምርመራ ቀጠሮ እና ክስ ከእስር ተለቀዋል። የቀድሞ ተቀዳሚ ሚኒስትሯ ስኮቲሽ ናሽናል ፓርቲ ወይም ኤስኤንፒ ፋይናንስ ላይ እየተደረገ ካለው ምርመራ ጋር በተያያዘ ነበር ትላንት የታሰሩት። ኒኮላ ስተርጅን በፖሊስ መርማሪዎች ጥያቄ ከቀረበባቸው በኋላ ነው ከእስር የተፈቱት።

ከእስር ከተፈቱ በኋላ በሰጡት አስተያየት "ምንም አይነት ያልተገባ ድርጊት እንዳልፈጸምኩኝ አውቃለሁ" ብለዋል። ፖሊስ ከእስር መፈታታቸውን በተመለከተ ለዘውድ ምክር ቤት እና ለዐቃቤ ሕግ ሪፖርት እንደሚያቀርብ ገልጿል። ፖሊስ ላለፉት ሁለት ዓመታት ለስኮትላንድ ሕዝበ ውሳኔ ዘመቻ የሚውል ከገለልተኛ አካላት ለስኮቲሽ ናሽናል ፓርቲ ወይም ኤስኤንፒ የተመደበው 660 ሺህ ፓውንድ የገባበትን ለማወቅ ምርመራ ሲያደርግ ቆይቷል።

የፖሊስ መኮንኖች ስተርጅን ከእስር ከመለቀቃቸው በፊት እሳቸውን ለመልቀቅ ወይም ክስ ለመመስረት በተመለከተ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እስከ 12 ሰዓታት የፈጀ ምርመራ አድርገዋል። ከዚያም ያለክስ እና ተጨማሪ ምርመራ አሰናብተዋቸዋል። ተጨማሪ ምርመራ እየተደረገበት ያለ ሰው ከእስር ቢለቀቅም ዳግም በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሊውል ይችላል።

ስተርጅን ከእስር መለቃቸውን ፖሊስ ባረጋገጠ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በትዊተር ገጻቸው ላይ መልዕክት አስተላልፈዋል። "ምንም እንዳላጠፋሁ እርግጠኛ ሆኜ ራሴን በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሳገኘው በጣም አስደንጋጭ እና አሳዛኝ ነው" ያሉት የቀድሞዋ ከፍተኛ ባለሥልጣን "አሁን ኤስኤንፒ እየተደረገ ያለው ምርመራ ለሰዎች አስቸጋሪ እንደ ሆነ አውቃለሁ። ብዙዎች እኔ ላይ እምነት ስላሳዩ አመሰግናለሁ። እኔ ኤስኤንፒንም ሆነ አገሬን የሚጎዳ ምንም ነገር አልፈጸምኩም" ብለዋል።

የስኮትላንድ ተቀዳሚ ሚኒስትር እና የኤስኤንፒ መሪ የነበሩት ስተርጅን ባለፈው የካቲት ነበር ሀምዛ የሱፍ በተባሉ ፖለቲከኛ የተተኩት። የቀድሞዋ ሚኒስትር ቀድሞ የእምነት ክህደት ቃላቸው ከሰጡ በኋላ በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ ተደርጎባቸዋል። ስተርጅን ከመታሰራቸው ወራት ቀደም ብሎ የኤስኤንፒ መሪ የነበሩት ባለቤታቸው ፒተር ሙሬል በቁጥጥር ስር ውለው ነበር። ባለቤታቸው በታሰሩበት ተመሳሳይ ቀን ቤታቸው በፖሊስ ብርበራ ተደርጎበታል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ለስልታዊ ትብብር ከፑቲን ጋር እንደሚሰሩ ቃል ገቡ



የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን ከሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ጋር "እጅ ለእጅ" ለመያያዝ ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል። ኪም ሁለቱ መሪዎች ኃያላን አገር ለመገንባት ያላቸውን የጋራ ዓላማ በስልታዊ ትብብር ለማጠናከር ቃል መግባታቸውን የሰሜን ኮሪያ የመንግስት መገናኛ ብዙሃን የሆነው ኬሲኤንኤ ዘግቧል።

ኪም ጆንግ ኡን የሩሲያ ብሄራዊ ቀንን ምክንያት በማድረግ ለፑቲን ባስተላለፉት መልዕክት፤ ከዩክሬን ጋር የሚያካሄዱት ጦርነት ትክክለኛ ውሳኔ መሆኑን አድንቀዋል። የፒዮንግያንግ መሪ ለሞስኮ "ሙሉ ድጋፍ እና አጋርነት" እንደሚሰጡ ገልጸዋል።

"ፍትህ እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ ነኝ። እናም የሩሲያ ህዝብ ለድል ክብር መስጠቱን ይቀጥላል" ሲሉ ኪም በመልዕክታቸው ተናግረዋል። ኪም ከሞስኮ ጋር "የቅርብ ስልታዊ ትብብር" ለማድረግ ጥሪ አቅርበዋል።

"ከሩሲያው ፕሬዚዳንት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን የሁለቱ አገራት ህዝቦች የጋራ ፍላጎት የሆነውን ኃያል አገር የመገንባት ታላቅ ግብ ለማሳካት በቅርበት እንተባበር" ሲሉም ተናግረዋል።

ሰሜን ኮሪያ ባለፈው ዓመት የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ከተጀመረ በኋላ ሞስኮን ደግፋ ከክሬምሊን ጋር የጠበቀ ግንኙነት ለመፍጠር ሞክራለች። ለዚህ እርምጃዋ የአሜሪካን እና የምዕራባውያንን ፖሊሲና ጣልቃ-ገብነትን ተጠያቂ ማድረጓን አል ዐይን ዘገባ ያመለክታል።

# በክልሉ 273 ሺህ አርሶአደሮች ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እየተጠቀሙ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል ከ273 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች የተለያዩ ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እየተጠቀሙ መሆኑን የሲዳማ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የቢሮው ኃላፊ አቶ መምሩ ሞኬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከ273 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች በቡና፣ በሰብል ልማት እና በተለያዩ የግብርና ስራዎች ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን እየተጠቀሙ ይገኛል፡፡

አርሶ አደሮቹ ለሰብል ልማት ትራክተር፣ ማጨጃ፣ መውቂያና ሌሎች ለኬሚካል መርጫ የሚያገለግሉ ዘመናዊ መሳሪያዎችን እየተጠቀሙ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በክልሉ ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀሙት አርሶ አደሮች 43 በመቶ ደርሰዋል ያሉት ኃላፊው፤ ሞዴል አርሶ አደሮች እየተጠቀሙት ያለውን ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂ ወደሌሎች አርሶ አደሮች ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ መምሩ ገለጻ፣ በክልሉ የእርሻ ስራ በበጋ፤ በበልግ እና በመኸር ወቅቶች የሚሰራ ሲሆን፤ ከ23 ሺህ ሄክታር በላይ የኩታ እርሻ መሬት በትራክተርና ዘመናዊ መሳሪያዎችን በመጠቀም እንደሚለማ ገልጸዋል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት በክልሉ የሚገኙ አርሶ አደሮች የተለመደውን ባህላዊ የአስተራረስ ዘዴ ብቻ ይከተሉ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ ግብርናውን ለማዘመን በተሰራው ስራ የተሻለ የቴክኖሎጂ፤ የምርጥ ዘርና ማዳበሪያ አጠቃቀም ልምድ እያደረገ እንደሚገኝ አመላክተዋል።



አቶ መምሩ ሞኬ

በሰብል ልማቱ ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አንጻር የኩታ ገጠም አስተራረስ ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል። በኩታ ገጠም እርሻ በቆሎ፣ ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ባቄላ እና አተር እየለሙ ይገኛል ብለዋል።

ኃላፊው እንዳስታወቁት፤ በበልግ እርሻ በ60 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ በቆሎ ለምቷል፡፡ የቴክኖሎጂ፣ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር አጠቃቀምን በማሻሻል በአንድ ሄክታር 50 ኩንታል በቆሎ ለማምረት እየተሰራ ይገኛል።

የግብርና ግብዓትና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ ያተኮሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በየጊዜው ለአርሶአደሩ እንደሚሰጡ አቶ መምሩ ተናግረዋል፡፡

የክልሉን የቡና ምርታማነት ለመጨመር አዳዲስ አሰራሮችን የማስተዋወቅ ስራ እየተከናወነ ይገኛል ያሉት ኃላፊው፤ በአንድ ሄክታር ይገኝ የነበረውን ስምንት ኩንታል የቡና ምርት በአሁኑ ወቅት በሔክታር ወደዘጠኝ ኩንታል ከፍ ማድረግ ተችሏል ብለዋል፡፡

በተቀረው የቡና ምርታማነት ማሳደግ ስራ ክልሉ ከ27 ሺህ ቶን በላይ ቡና ለዓለም ገበያ እየቀረበ እንደሚገኝ አቶ መምሩ አስታውቀዋል።

# ለአገራዊ ምክክሩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የአገር ሽማግሌዎች ከህዝቡ ጋር የሚኖሩ በመሆናቸው ከማህበረሰቡ ጋር የመገናኘት እድል እንዳላቸው የገለጹት አቶ ሰዲቃ፤ ህዝቡ ስለሚደረገው ምክክር በጎ አመለካከት እንዲኖረው ህዝቡን ማስተማር አለብን ብለዋል፡፡

የተለያዩ መድረኮች ተፈጥሮላቸው የአገር ሽማግሌዎቹ ስለአብሮነት፣ስለመከባበር እና ከቂም በቀል መቆጠብ እንደሚያስፈልግ ህዝቡን የማስተማር እና ለምክክሩ የማዘጋጀት ኃላፊነት እንዳለባቸውም ጠቁመዋል፡፡

የአገር ሽማግሌዎች ከምክክር ኮሚሽኑ ጋር ተደጋጋሚ ግንኙነቶች ማድረጋቸውን የጠቆሙት የሀገር ሽማግሌው፤ የተሳታፊ ልየታን በሚመለከት እንዲሁም ምክክሩ በተቻለ ፍጥነት መካሄድ እንዳለበት ሀሳብ መስጠታቸውንና ከኮሚሽኑ ጋር ተባብረው በጋራ ለመስራት መስማማታቸውን ተናግረዋል፡፡

በመግባባት ፣በይቅር ባይነትና በመተሳሰብ ምክክሩን ለማጠናቀቅ ህዝቡ ከምንም አይነት የፖለቲካ አስተሳሰብ ነጻ ሆኖ በወኪሎቹ አማካኝነት መወያየት እና ችግሮችን መፍታት አለበት ያሉት አቶ ሰዲቃ፤ መንግስትም በአገሪቷ ያለውን ያለመግባባት ችግር እንዲፈታ ኮሚሽኑን ማቋቋሙ መልካም ቢሆንም ለስኬታማነቱም እስከ መጨረሻው ከጎኑ መቆም እንደሚጠበቅበት ገልጸዋል፡፡

ሌላኛው የአገር ሽማግሌ ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ በበኩላቸው፤ ቀደም ባለው ጊዜ የነበሩ አለመግባባቶችን ይፈቱ የነበሩት የአገር ሽማግሌዎች መሆናቸውን አስታውሰው፤ በአገራዊ ምክክሩም የጋራ ችግሮችን ለመለየት፣የጋራ መፍትሄዎችን ለማበጀት እና የምክክሩን ሂደት ለማስተካከል የአገር ሽማግሌዎች የጎላ ሚና መጫወት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

የአገር ሽማግሌዎች የአካባቢውን ባህሪ በቅርበት የሚያውቁ በመሆኑ ያሉትን ችግሮች በሚገባ ይረዳሉ ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ማህበረሰቡን በማስተባበር ለምክክሩ ስኬታማነት መስራት ይጠበቅብናል ብለዋል፡፡

ምክክሩእንደአገርያሉብንንየኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የማህበረሰብ ችግሮች በአጠቃላይ ተገንዝቦ ችግሮች የሚፈቱበት መሆን እንዳለበት ጠቁመው፤ ኮሚሽኑ የሌሎች አገራት ተሞክሮዎችን በመመልከት ስኬታማ ስራ ይሰራል ብለው እንደሚጠብቁ ገልጸዋል፡፡

የምክክር አጀንዳ ልየታ ላይ ህዝቡ በግልጽ ሊወያይባቸው የሚፈልጋቸውን ጉዳዮች እንዲያመጣ ማበረታታት እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ ማህበረሰቡም ችግሩን በሚገባ በመለየት አጀንዳዎቹን ለምክክር ማቅረብ እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት የአገር ሽማግሌዎች ግጭቶችን በመፍታት ችግሮች እንዳይባባሱ ሲሰሩ መቆየታቸውን ያስታወሱት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ፤ አሁንም በምክክሩ የላቀ ድርሻ እንዲኖራቸው እየተመካከሩ አቅጣጫ በማሳየት የኢትዮጵያን ችግር ይፈታል ተብሎ ተስፋ የተጣለበትን አገራዊ ምክክር ማገዝ ይጠበቅብናል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ስፖርት



## ዋልያዎቹ ዝግጅታቸውን በአዳማ ያደርጋሉ

ዓስማየሁ ግዛው

ለ2024ቱ የኮትዲቯር አፍሪካ ዋንጫ የማለፍ ተስፋቸው አጣብቂኝ ውስጥ የገባው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) የምድባቸውን አምስተኛ የማጣሪያ ጨዋታ የፊታችን ሰኔ 13 ያደርጋሉ:: ለዚህም ጨዋታ ዝግጅት ለ23 ተጫዋቾች ጥሪ ተደርጓል:: የዋልያዎቹ ጊዜያዊ አሰልጣኝ ኢንስትራክተር ዳንኤል ገብረማርያም ጥሪ ያደረጉላቸው ተጫዋቾች ከትላንት ጀምሮ ሪፖርት በማድረግ ዝግጅት እንደጀመሩም አሳውቀዋል::

በኮትዲቯር አስተናጋጅነት ለሚካሄደው 34ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ በምድብ አራት የተደለደለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አምስተኛ የምድብ ጨዋታውን ከማላዊ አቻው ጋር ያደርጋል:: ይህን የማጣሪያ ጨዋታ ከአሰልጣኝ ውበቱ አባተ የብሔራዊ ቡድኑን ዋና አሰልጣኝነት ቦታ የተረከቡት ኢንስትራክተር ዳንኤል የሚመሩ ይሆናል::

በ12 ምድቦች ተከፍሎ በመካሄድ ላይ በሚገኘው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ኢትዮጵያ በምድብ አራት ከጊኒ፣ ማላዊና ግብፅ ጋር መደልደላ ይታወቃል:: እስካሁን አዘጋጇን ኮትዲቯርን ጨምሮ ስድስት ሀገራት ወደ አፍሪካ ዋንጫ ማለፋቸውን አረጋግጠዋል:: ሌሎች የተቀሩት ኃላፊ ሀገራት በቀሩት ሁለት ምድብ ማጣሪያ ጨዋታዎች የሚለዩም ይሆናል:: ኢትዮጵያም የማለፍ ዕድሏ አጣብቂኝ ውስጥ ቢገባም የማጣሪያ ጨዋታዋን ከማላዊ ብሔራዊ ቡድን ጋር ታደርጋለች::

ኢትዮጵያ በምድቡ ካደረገቻቸው አራት ጨዋታዎች ማሸነፍ የቻለችው አንዱን ሲሆን በሶስቱ



ጥሪ የተደረገላቸው 23 ተጫዋቾች ከትናንት ጀምሮ በአዳማ ይዘጋጃሉ፣

ትሸንፋለች:: ብቸኛውን ድሏንም መቀዳጀት የቻለችው የመድረኩን የ7 ጊዜ አሸናፊ ግብጽን ከጨዋታ ብልጫ ጋር 2ለ0 በሆነ ውጤት በመርታት ነበር:: ኢትዮጵያ ምንም እንኳን በመጀመሪያ የምድብ ጨዋታ በማላዊ በጠባብ ውጤት ብትሸነፍም በሁለተኛው የምድብ ጨዋታ ግብፅን በመርታቷ የማለፍ ተስፋዋን አለምልማ የምድቡ መሪ እስከ መሆን ደርሳ ነበር:: በተከታታይ ከጊኒ ጋር ያደረገቻቸውን የምድቡን ሶስተኛና አራተኛ ጨዋታዎች በመሸነፏ ግን የማለፍ እድሏ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተል:: ይህም በምድቡ አምስተኛ ጨዋታ ብዙ ተስፋ እንዳይደረግ አድርጓል:: ኢትዮጵያ በነዚህ ጨዋታዎች በተጋጣሚዎቿ መረብ ላይ 5 ጎሎችን አስቆጥራ 7 ጎሎች ተቆጥሮባታል:: በዚህም መሰረት በ3 ነጥብና በ2 የግብ እዳ የምድቡ ግርጌ ላይ ተቀምጣለች::

ኢትዮጵያ የምድብ አምስተኛ ጨዋታዋን ሰኔ 13 ከማላዊ ጋር በገለልተኛ ታደርጋለች:: ምድቡን አንደኛና ሁለተኛ ሆኖ በመምራት ላይ የሚገኙት ግብፅና ጊኒ እንዲሁ እርስ በእርሳቸው ይገናኛሉ:: ሁለቱ አገራት ምድቡን በእኩል ነጥብ በግብ ክፍያ ተበላልጠው እየመሩ ሲሆን በአቻ ውጤት ጨዋታቸውን የሚጨርሱ ከሆነ አንድ ጨዋታ እየቀራቸው ከምድቡ ተያይዘው የሚያልፉ ይሆናል:: የኢትዮጵያም የማለፍ ተስፋ በጣም ጥቂት ሲሆን ከሁለቱ አንዳቸው ሁለት ጨዋታ መሸነፍ እና ኢትዮጵያ ሁለት ቀሪ ጨዋታዎቿን በሰፊ ውጤቶች ማሸነፍ የግዴታ ይሆናል::

ኢትዮጵያ በሀገሪቱ ውስጥ አንድም የካፍ ደረጃን የሚያሟላ ስቴድየም ባለመኖሩ ሶስቱን የምድብ የማጣሪያ ጨዋታዎቿን በተለያዩ ሀገራት በመዘዋወር እያደረገች እንደሆነ ይታወቃል:: አምስተኛውም የምድብ ማጣሪያ ጨዋታ እንዲሁ በሌላ ሀገር ስቴድም ይካሄዳል:: ለጨዋታውም ዝግጅት እንዲረዳ 7 አዳዲስ ተጫዋቾችን በማካተት ለ23 ተጫዋቾች ጥሪ ተደርጓል:: የኢትዮጵያ ቤትኪንግ ፕሪሚየር ሊግ መሪ ቅዱስ ጊዮርጊስና ባህርዳር ከነማ እያንዳንዳቸው አምስት አምስት ተጫዋቾችን አስመርጠዋል::

ብሔራዊ ቡድኑ ሶስት ግብ ጠባቂዎችን በማካተት (ሰይድ ሀብታሙ ከባህርዳር ከተማ፣ ባህሩ ነጋሽ ከቅዱስ ጊዮርጊስና ቢኒያም ገነቱ ከወላይታ ድቻ) መርጧል:: የተከላካይ ክፍሉ ደግሞ ስምንት ተከላካዮችን (ዓለም ብርሃን ይግዛው፣ ሄኖክ አዱኛ፣ ረመዳን ሱፍ፣ ፍራኦል መንግስቱ፣ ሚሊዮን ሰለሞን፣ አስቻለው ታመነ፣ አማኑኤል ተረፈንና ያሬድ ባዬን) አካቷል:: በአማካይ ክፍሉ 7 ተጫዋቾች የተካተቱ ሲሆን (አለልኝ አዘነ፣ አማኑኤል ዮሐንስ፣ ሽመልስ በቀለ፣ አበባው ሀጂሶ፣ ከነአን ማርክነ፣ ቢኒያም በላይ እና ወገኔ ገዛኸኝ) መካተታቸው ታውቋል:: የአጥቂ ስፍራ ለአምስት ተጫዋቾችን ጥሪ የተደረገ ሲሆን ዮሴፍ ታረቀኝ፣ ብሩክ ሙሉጌታ፣ ዱሬሳ ሹቢሳ፣ ሀብታሙ ታደሰን አቤሎ ማሙሽ ጥሪ የተደረገላቸው ተጫዋቾች ናቸው::

ዋልያዎቹ ዝግጅታቸውን በአዳማ እንደሚያደርጉ የተገለጸ ሲሆን ጊዜያዊ አሰልጣኙ ኢንስትራክተር ዳንኤል የሚመሩት ቡድን በረዳት አሰልጣኝነት የባህርዳር ከነማው አሰልጣኝ ደግአረገ ይግዛው፣ የግብ ጠባቂዎች አሰልጣኝ ውብሸት ደሳለኝን አካቷል::